# የእይታና የትወና ጥበባት



## የተማሪ መጽሐፍ

## 4ኛ ክፍል

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# የእይታና የትወና ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 4ኛ ክፍል


**አስማምቶ አዘጋጆች፡-**

ምህረቱ ዋሴ      ታሪኳ ተሰማ

ታምራት አብርሃም

**አርትኦት፡-** ፍላጎት ታደሰ

**ሰዓሊ፡-** ምህረቱ ዋሴ

**የሙዚቃ ኖታ ጸሐፊ፡-፡-** ታሪኳ ተሰማ

**የጥራት ተቆጣጣሪ**

ተክለማሪያም ጥላሁን      ተዋበ ታደሰ

**አጽዳቂዎች(ቫሊዴተር)**

ፍቅሩ አርፋሶ      አሰጋኸኝ ጉዬ

አረጋ አሰፋ      ሰውነት ቶማስ

ለምለም ደግፌ

**ሌያውት ዲዛይን፡-** ኃይለማርያም መለሰ



የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# © የቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ተዘጋጅቶ አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል።

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ነው።

# ማውጫ


**መግቢያ ........................................................................ i**

**ምዕራፍ አንድ: ምልከታ ....................................................... 1**

1.1. መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን በቀላል ስልተ-ምቶች መረዳት .....2
1.2. ዝርግ ቅርፆችን እና ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት ማጥናት ..............7
1.3. ምጥን ተውኔቶችን መረዳት ......................................................15
1.4. የቁምና አግዳሚ ፎቶግራፍ አነሳስ አይነቶችን መረዳት ................15

**ምዕራፍ ሁለት: የግልና የቡድን ትግበራዎች .......................27**

2.1. የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ (ስታፍ) እና ቁልፎች (ክሌፍ) ................28
2.2. ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜዎች .............................................................33
2.3. ኮላጅን ለስላሳ/ሸካራ በሆኑ አካባቢያዊ ቁሳቁሶች መስራት .............35
2.4. ቅርፆች ፣ ለስላሳነትና ሸካራነት ..................................................43
2.5. ድምፅ-አልባ ተውኔትና ግለ-ተውኔት (መነባንብ)..........................48

**ምዕራፍ ሦስ: የትውን እና የእይታ ጥበባት ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጠቀሜታ ..........................................54**

3.1. የትውን እና የእይታ ጥበባት በማህበረሰቡ ታሪክ እና ባህል ውስጥ ያለው ሚና ...................................................................55

**ምዕራፍ አራት: አድናቂነት ..........................................69**

4.1. የትውን እና የእይታ ጥበባት በአፈፃፀምና በምስል ጥበባት ውስጥ ደጋግሞ የመለማመድ ውጤት ..............................................70

4.2. ሃገር በቀል የቤት አሰራርን እና ማስጌጥን፤ የሙዚቃ ጨዋታዎችንና ውዝዋዜዎችን እንዲሁም ድራማዊ እንቅስቃሴዎችን እውቅናና አድናቆት መስጠት ..............................................................76

**ምዕራፍ አምስት: የትውን እና እይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማዛመድ ..........................89**

5.1. የአይታና የትውን ጥበባት እርስ በርስ ያላቸው ዝምድና ............90

5.2. የእይታና የትውን ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማገናኘት ...................................................................91

**ዋቢ መጽሀፍት ....................................................110**

# መግቢያ

በዚህ የአራተኛ ክፍል የእይታ እና የትውን ጥበባት መጽሀፍ ተማሪዎች ስለ ስዕል ፣ ሙዚቃ፣ ዳንስ እና ተውኔት በቂ ግንዛቤ እና ችሎታ እንዲያገኙ ያግዛቸዋል:: ይህ መጽሀፍ በአምስት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን በውስጡም ስለ ስነ-ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ተውኔት በስፋት እና በጥራት ትንታኔ ከመስጠት በተጨማሪ በቂ ክህሎት እንዲያገኙ የተግባር ስራዎችን አካቶ የያዘ ነው:: በዋናነት የማየት ፣ የፈጠራ ችሎታን የማሳደግ ፣ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር የማገናኘት እና ከአካባቢያዊ እውቀቶች ጋር በማዛመድ ሙያዊ ብቃታቸውን እንዲያዳብሩ ታሳቢ ሆኖ የተዘጋጀ መጽሀፍ ነው:: ተማሪዎች ይህንን የአራተኛ ክፍል መጽሀፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ የሚከተሉትን የብቃት አሀዶች ያገኛሉ፦

- ዝርግና ባለሶስት አውታር ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት ይስላሉ ፣ የሙዚቃ ኖታዎችን እስከ ሩብ ኖታ ድረስ ይገልፃሉ
- ድምጽ-አልባ ትወናዎችን ፣ መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን ይከውናሉ
- የቁምና አግዳሚ ፎቶ ግራፍ አነሳስ አይነቶችን ያብራራሉ
- ተንቀሳቃሽ ምስሎችንና ፎቶዎችን በመመልከት መልዕክቶችን ይረዳሉ
- በሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ ላይ የሙዚቃ ጽሁፍን (መስመርንና ክፍት ቦታን) ከቁልፍ የኖታዎች ቦታ ጋር በማገናኘት (የረዳት መስመሮችን በማካተት) ይረዳሉ
- የቤተሰብ የአብነት እንቅስቃሴዎችን በዘፈንና በውዝዋዜ ያሳያሉ
- ንድፎችን በመስራት የተለያዩ ቀለሞችን በመቀባትና በኮላጅ መልክ በመለጠፍ ይለማመዳሉ
- ሃገር በቀል የቤት አሰራርን ፣ ማስጌጥንና የሙዚቃ ጨዋታዎችን ያውቃሉ ፣ ያደንቃሉ
- በድምፅ-አልባ ተውኔትና በግለ-ተውኔት (መነባንብ) እንዲሁም በስዕልና በፎቶ መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃሉ
- የትውን እና የእይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያዛምዳሉ
- የመዝሙሮችን ፣ የዝርግ ቅርጾችንና የቀለማትን አስፈላጊነት ይረዳሉ
- ከዛፎችና እንስሳት እንቅስቃሴ በመነሳት ውዝዋዜዎችን ያስመስላሉ

# ምዕራፍ አንድ

## ምልከታ

### መግቢያ

በምዕራፍ አንድ አካባቢያችንን በደንብ በመመልከት ለተለያዩ ፈጠራዎች መነሻ ሃሳብ እንድናገኝ ያግዛል:: ተፈጥሮአዊ ነገሮችን በመመልከት የተራራዎችንና የዛፎች እንቅስቃሴዎች ፣ የአበቦችን ቀለማት ፣ የወንዞችና የፏፏቴዎችን ድምፅ ፣ የእንሥሣት አይነቶችንና ባህሪያትን ከትውን እና የእይታ ጥበባት ጋር በማዛመድ ለተለያዩ ፈጠራዎች መነሻ እንዲሆን አካባቢን ማወቅ ትልቅ ሚና አለው:: አካባቢያችንን በሚገባ በተረዳን ቁጥር ለሰዕል ፣ ለሙዚቃ ፣ ለቲያትር ፣ ለድርሰት እንዲሁም ለሌሎች የፈጠራ ውጤቶች ጥሩ ግብዓቶችን እናገኛለን:: በዓለም ላይ እጅግ ተፅዕኖ ፈጣሪ የምንላቸው ሰዎች የሰሯቸው ፈጠራዊ ስራዎች መነሻቸው ተፈጥሯዊ ነገሮች ናችው:: ለምሳሌ አውሮፕላን ከወፎችን እንቅስቃሴ በመነሳት ፣ መኪና ባለ አራት እግር እንሰሳትን በመመልከት እንዲሁም ባቡር የተለያዩ በደረታቸው የሚሳቡ እንሣትን መሰረት በማድረግ የተሰሩ የፈጠራ ስራዎች ናቸው:: ስለዚህ አካባቢያችንን የበለጠ በተረዳንና ባወቅን መጠን የተለያዩ ችግር ፈቺ ምርምሮች ለመስራት የመነሻ ሃሳብ እናገኛለን::

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ዝርግና ባለሶስት አውታር ቅርፃችን በተለያዩ ቀለማት ይለያሉ
- የሙዚቃ ኖታዎችን እስከ ሩብ ኖታ እና ሩብ እረፍት ድረስ ይገልፃሉ
- ድምጽ-አልባ ትወናዎችን ፣ መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን ይከውናሉ
- የቁምና አግዳሚ ፎቶግራፍ አነሳስ አይነቶችን ለይተው ያውቃሉ
- በቀላል ምት መዝሙርን እና ውዝዋዜን መዘመር እና መወዛወዝን ይረዳሉ

## 1.1. መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን በቀላል ስልተ-ምቶች መረዳት

### መግቢያ

መዝሙሮችን በቀላል ምቶች መረዳት ማለት ተማሪዎች የተለያዩ ኖታዎችን ተጠቅመው በቀላሉ መዝሙሮችን መዘመር እንዲችሉ ማስቻል ማለት ነው:: ይህም ማለት መዝሙሮችን በቀላሉ በአካባቢያችን ከሚገኙ የተፈጥሮ እንቅስቃሴዎች ጋር ማገናኘት ማለት ነው:: መዝሙሮችን በቀላል ስልተ-ምቶች የምንረዳው መዝሙሮችን በምንሰማበት ጊዜ እኩል በማጨብጨብ ፣ በእግራችን መሬቱን እየመታን በማዳመጥ እንዲሁም ጭንቅላታችንን በቀስታ ከፍና ዝቅ እያደረግን በመቁጠር ቀላል ስልተ-ምቶችን በመጠቀም ነው::

መዝሙሮችን በቀላል ስልተ-ምቶች መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች የተለያዩ ኖታዎችን በማየትና በመጫወት መዝሙሮችን ለመዘመር ሲችሉ ነው:: ለዚህም መዝሙሮችን በቀላሉ በአካባቢያችን ከሚገኙ የተፈጥሮ እንቅስቃሴዎች ጋር ማገናኘት እንድንዘምር ለማድረግ ያግዛል::

## ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ

- ተማሪዎች መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን በቀላል ስልተ-ምቶች ይረዳሉ

- የተለያዩ አከባቢዎች ላይ በቀላል ስልተ-ምቶች የሚዘመሩ መዝሙሮች እና ውዝዋዜዎችን ለይተው ያውቃሉ

## ማነቃቂያ

- የምታውቁትን መዝሙር በማጨብጨብ ዘምሩ

## ሀ. መዝሙሮችን በቀላል ስልተ-ምቶች መረዳት

መዝሙሮችን በቀላል ምቶች መረዳት ማለት በአካባቢያችን እንዲሁም በተለያዩ ትምህርት ቤቶችና የሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ልንሰማቸውና ልናያቸው የምንችላቸውን ዜማዎች በግልም ሆነ በጋራ መዘመር ማለት ነው::


በአካባቢያችንየምናዘወትራቸውንነገሮችበማምጣትበመዘመርልንለማመድባቸው እንችላለን:: በአከባቢያችን የተለያዩ ቀላል ምቶችን በመጠቀም የምንዘምራቸውን መዝሙሮች በክፍል ውስጥ መዘመር እንችላለን:: ከእነዚህም መካከል ልጆች በጋራ በሚጫወቱበት ጊዜ በተደጋጋሚ የሚዘምሯቸውን መዝሙሮች እያነሳን መዘመር እንችላለን::

**ምሳሌ 1.1-**

**ጭል ጭል**

ጭል ጭል ጭል ጭል ትንሿ ኮከብ
ይደንቀኛል አንቺን ሳስብ
ከፍ ብለሽ ከዓለም በላይ
ልክ እንደ እንቁ በሰማይ ላይ
ደማቅ ጮራዋን ፈንጥቃ
ጭል ጭል ጭል ጭል ሌቱ አበቃ

ምሳሌ፡-　　　　　　　　　|ጭል ጭል




ምስል 1.1- ጭል ጭል መዝሙር በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ

## ለ. ውዝዋዜዎችን በቀላል ስልተ-ምቶች መረዳት

ውዝዋዜን በቀላል ስልተ-ምቶች ልንረዳ የምንችለው በምንጫወትበት እና መዝሙር በምንዘምርበት ጊዜ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ እና በመወዛወዝ ነው፡፡

ውዝዋዜዎችን በቀላል ምቶች ለመረዳት በትምህርት ቤቶች ውስጥ ክብ በመስራት እንዲሁም በመዘመር መለማመድ እንችላለን፡፡

ምሳሌ2፡-

### ልጅ ለመፈለግ

ልጅ ለመፈለግ መተናል ዛሬ በማለዳ
ማንን ትፈልጋላችሁ ዛሬ በማለዳ
ሃናን እንፈልጋታለን ዛሬ በማለዳ
እሷን መጥቶ የሚወስዳት ማን ጎበዝ አለና
ሩት ጎበዝ አለችን

የኛ ልጅ በርቺ በርቺ እንዳትረቺ
የኛ ልጅ በርታ በርታ እንዳትረታ

## መልመጃ 1.1

◆ በአካባቢያችሁ ከሚገኙ እንስሳቶችና እፅዋቶች እንቅስቃሴ በመነሳት የተለያዩ ውዝዋዜዎችን በቀላል ስልተ-ምቶች እየተወዛወዛችሁ ተለማመዱ::

## 1.1.1. የሙዚቃ ኖታዎች እስከ ሩብ ኖታ እና ሩብ እረፍት ድረስ ያሉ ምልክቶች

በዚህ ርዕስ ተማሪዎች የሙዚቃ ኖታዎችን እና የእረፍት ምልክቶችን ተማሪዎች ትረዳላችሁ:: ለዚህም ድምፆችን እና የእረፍት ምልክቶችን ታ ታ በማለት እንዲሁም በዝምታ ለመረዳት ትሞክራላችሁ:: በሶስተኛ ክፍል የሙዚቃ ኖታዎችን ስለ ተማራችሁ በዚህ የ4ኛ ክፍል ቆይታችሁ ደግሞ የሙዚቃ ኖታዎችን እና እረፍቶችን ማለትም ሙሉ ኖታ (4 ምት ያለው) ፣ ግማሽ ኖታ (2 ምት ያለው) ፣ ሩብ ኖታ (1 ምት ያለው) እና ተመጣጣኝ የእረፍት የጊዜ ቆይታቸውን ትረዳላችሁ:: የኖታ እና የእረፍት ምልክቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል::

## 1.1.2. የሙዚቃ ኖታ እና የእረፍት ምልክቶች እስከ ጊዜ ቆይታቸው

| የኖታው ስም | የኖታ (የድምፅ) ምልክት | የእረፍት (ድምፅ-አልባ) ምልክት | የጊዜ ቆይታቸው |
|---|---|---|---|
| ሙሉ ኖታ | 𝅝 | 𝄻 | 4 |
| ግማሽ ኖታ | 𝅗𝅥 | 𝄼 | 2 |
| ሩብ ኖታ | 𝅘𝅥 | 𝄽 | 1 |

ምስል1.2- የሙዚቃ ኖታ እና የረፍት ምልክቶች

ከላይ የተቀመጡት የኖታ ስሞች ፣ የኖታ ምልክቶች እንዲሁም የእረፍት ምልክቶች የቆይታ ጊዜን ያመለክቱናል፡፡ በዚህም መሰረት የዜማ እና የእረፍት ጊዜን በዝርዝር እናያለን፡፡

- ሙሉ ኖታ (ሙሉ ባለ ድምፅ ኖታ)- 

ሙሉ ኖታ የጊዜ ቆይታው 4 ምት በድምጽ ሲሆን ይህ ማለት በእጃችን አራት ጊዜ ማጨብጨብ ማለት ነው፡፡ የተሰጠን የጊዜ ገደብ እስኪያልቅ ድረስ እያጨበጨብን እንቆያለን ማለት ነው፡፡

- ሙሉ እረፍት (ሙሉ ድምፅ አልባ ኖታ) 

ሙሉ እረፍት የሚቆየው የጊዜ ቆይታው ልክ እንደ ሙሉ ኖታ 4 ጊዜ ሆኖ የሚለየው በዝምታ ስለሚቆጠር ብቻ ነው፡፡

- ግማሽ ኖታ (ግማሽ ባለ ድምፅ ኖታ) 


ግማሽ ኖታ የሚቆየው የጊዜ ቆይታው 2 (የሙሉ ኖታ እኩሌታ) ሲሆን ይህ ማለት በእንጃችን በማጨብጨብ ሁለት ጊዜ እንቆጥራለን እየደጋገምን በመዘመር የቆይታውን ጊዜ እንገልፃለን፡፡

- ግማሽ እረፍት (ግማሽ ድምፅ አልባ ኖታ) 

ግማሽ እረፍት የሚቆየው የጊዜ ቆይታው ልክ እንደግማሽ ኖታ 2 (የሙሉ ኖታ እኩሌታ) ሲሆን ከግማሽ ኖታ የሚለየው የተሰጠን የጊዜ ቆይታ ገደብ እስኪያልቅ ድረስ በፀጥታ (በዝምታ) በውስጣችን እንቆጥራለን፡፡

- ሩብ ኖታ (ሩብ ባለድምፅ ኖታ) 

ሩብ ኖታ የሚቆየው የጊዜ ቆይታ 1 ምት በድምጽ (የግማሽ ኖታ እኩሌታ) ሲሆን ይህ ማለት ለምሳሌ ያህል አንድ ጊዜ በእጃችን ስናጨበጭብ ማለት ነው፡፡

- ሩብ እረፍት (ሩብ ድምፅ አልባ ኖታ) 


ሩብ እረፍት የሚቆየው የጊዜ ቆይታ 1 ምት በዝምታ (የግማሽ ኖታ እኩሌታ) ሲሆን ከሩብ ኖታ የሚለየው የተሰጠን የጊዜ ቆይታ እስክያልቅ ድረስ በፀጥታ

በልባችን ስለምንቆጥር ነው።

### መልመጃ 1.2

- ተማሪዎች ከ ሙሉ ኖታ እና ሙሉ ረፍት እስከ ሩብ ኖታ እና ሩብ እረፍት ድረስ የጊዜ ቆይታቸውን በመፃፍ ተለማመዱ

- ከታች የተቀመጡ የኖታና የረፍት ምልክቶችን በማንበብ ተለማመዱ



## 1.2. ዝርግ ቅርፃችን እና ቅርፃችን በተለያዩ ቀለማት ማጥናት

### መግቢያ

በዚህ ርዕስ ስር ስለ ዝርግ ቅርፃች ባህሪ እና አይነቶች በተጨማሪም የተለያዩ ቀለማቶች መለየትን እንማራለን። ዝርግ ቅርፃችን በተለያዩ ቀለማት የምናጠናው በአዕምሮአችን ውስጥ ቶሎ እንድንለምዳቸው ሲሆን ቀለም መቀባት ስንጀምር ደግሞ የማቅለም ችሎታችንን ለመጨመር ነው።

### ከርዕሱ የሚጠበቁ የብቃት አሃዶች

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ

- ስለ ዝርግ ቅርፃች ባህሪያት ያጠናሉ
- ስለ ተፈጥሯዊ እና ሰውሰራሽ ዝርግ ቅርፃች ለይተው ያውቃሉ
- ስለ ቅርፃች ምንነትና ባህሪያት ያውቃሉ

### የማነቃቂያ ጥያቄ


- በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ የሚገኙ የተለያየ አይነት ቅርጽ እና ቀለም ያላቸውን ነገሮች ዘርዝሩ

## 1.2.1.ዝርግ ቅርፆች


ዝርግ ቅርፅ የሚፈጠረው አንድ መስመር ከተነሳበት ነጥብ ዞሮ ሲገጥም ነው፡፡ ዝርግ ቅርፅ (two dimensional shapes) በቁመትና በርዝመት ላይ ብቻ የተወሰነ ነው ስንል ጥልቀት የሌለው መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ እነዚህም ነገሮች ግድግዳ ላይ ፣ ወረቀት ላይ ፣ መሬት ላይ ወይም በማንኛውም ጠፍጣፋ ሰሌዳ ላይ ተስለው ልናገኛቸው እንችላለን፡፡ ሁለት አይነት ዝርግ ቅርፆችን እናገኛለን፡፡ እነርሱም ሰውሰራሽ እና እና ተፈጥሮአዊ ዝርግ ቅርፆች ናቸው፡፡

### ሀ. ሰውሰራሽ ዝርግ ቅርፆች (Geometric shapes)

እነዚህ ዝርግ ቅርፆች የታወቀ ቁመት እና ርዝመት ያላቸው ሲሆኑ በቀላሉ ዙርያቸውን ፣ አጋማሻቸውን ፣ ስፋታቸውን ማስላት እና ማወቅ እንችላለን፡፡ ለምሳሌ ክብ ፣ ሶስት ማእዘን ፣ ሬክታንግል ፣ ትራፒዝየም እና ፓራሌሎግራምን መጥቀስ እንችላለን፡፡





ምስል 1.3- ሰውሰራሽ ዝርግ ቅርፆች




ምስል 1.4- ዝርግ ቅርፆችና ቀለማት


## ለ. ተፈጥሮአዊ ዝርግ ቅርፆች (Organic Shapes)

ተፈጥሮአዊ ዝርግ ቅርፆች የምንላቸው የታወቀ ስምም ሆነ ቅርፅ የሌላቸው በተፈጥሮ የተገኙ ቅርፆች ናቸው፡፡ እነዚህም በተፈጥሮ የተገኙ ሰማይ ላይ ያለ የዳመና ቅርፅ፣ የዛፎች ውጫዊ ቅርፆች፣ እንዲሁም የተለያዩ ድንጋዮችን ውጫዊ ቅርፆችን መጥቀስ እንችላለን፡፡




ምስል 1.5- ተፈጥሯዊ ዝርግ ቅርፆች

ዝርግ ቅርፆችን እና ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት ስንለማመድ የመሳል፣ የማስታወስ እንዲሁም የማገናዘብ ችሎታችን ይጨምራል:: የተለያዩ ዝርግ ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት መቀባት እና ማጥናት ስንል ንድፎችን በመሳል ቀለም መቀባትን ለመረዳት ነው:: የመስመሮችን እንቅስቃሴ ጠብቀን እንዴት ቀለም መቀባት እንደምንችል እናያለን:: ባለሁለት አውታረ-መጠን ቅርፆችን ቀለም ስንቀባ ጥንቃቄን እና ውበትን በማሰብ ወጥ የሆኑ ቀለማትን በእኩል መጠን መቀባት ያስፈልጋል:: ስለዚህም ሁለት ነገሮችን ባንድ ላይ መስራትና መለማመድ እንችላለን:: የመጀመሪያው ቅርፆችን በትክክል መሳል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቀለማቶችን መቀባት ነው:: ቅርፆችን የተለያዩ ቀለማትን በመቀባት የምንማረው በቀላሉ ለማስታወስ ስለሚያግዘን ነው::




ምስል 1.6- ዝርግ ቅርፆች በተለያዩ ቀለማት ማጥናት

በሌላ በኩል አንድን ክብ ፣ ሬክታንግል ወይም ሶስት ማዕዘን ብዙ ቦታ ከፋፍለን ስንቀባ እንዴት በጥንቃቄ መቀባት እንዳለብን ስናስብ ፣ የመፍጠር እና የማገናዘብ ችሎታችንን ከፍ ለማድረግ ያግዘናል:: በአንድ ክብ ወስጥ ክፍልፋዮቹን በተለያዩ ቀለማት ማቅለም ደግሞ ሂሳብና የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን እያገናኘን ለመማር ያግዘናል:: እንዲሁም በምስሉ ላይ ቀለም የተቀባው ከሙሉ ቅርጹ ውስጥ ስንት እጅ እንደሆነ ሂሳባዊ በሆነ ስሌት በማስለት ከሂሳብ ትምህርት ጋር የሚኖራችሁን ግንኙነት ማጠናከር ያስችላል::



ምስል 1.7- በዝርግ ቅርፆች ውስጥ ያሉ ክፍልፋዮችን ቀለም መቀባት መለማመድ



ምስል 1.8- የዝርግ ቅርጽ ክፍልፋዮችን በተለያዩ ቀለማት በመቀባት መለማመድ

መልመጃ 1.3


- ተማሪዎች መምህራችሁ የኢትዮጵያን ካርታ ስለው የተለያዩ ክልሎችን በተለያየ ቀለም እየቀቡ ያሳይዋችኋል፡፡ ተማሪዎችም መምህራችሁ ዝርግ ቅርፆችን እንዴት እንደሚስሉ እና ቀለም እንደሚቀቡ በትክክል በመመልከት ደግማችሁ ሳሉ

## 1.2.2.ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት ማጥናት


በዚህ ንኡስ ርዕስ ተማሪዎች ዝርግ ቅርፃችን እንዴት ቀለም መቀባት እንደምንችል እንረዳለን፡፡ የዝርግ ቅርፃችን ባህሪ ከመረዳት በተጨማሪ ቅርፃችን ለይተን ለማወቅ ያግዘናል፡፡ ቅርፅ ስንል ከቁመትና ርዝመት በተጨማሪ ይዘት ወይም ጥልቀት ያለው በመሆኑን እንዲሁም ራሳቸውን ችለው መቀመጥ የሚችሉና ከተለያዩ አቅጣጫዎች ልንመለከታቸው ስንችል ነው፡፡ አንድን ቅርፅ ከፊት ለፊት ፣ ከጎን እንዲሁም ከላይ ሆነን ልንመለከተው እንችላለን፡፡ በመሰረታዊነት የዝርግ ቅርፅ እና ቅርፅ ልዩነት የይዘት/ጥልቀት መኖር እና አለመኖር ነው፡፡ ልክ እንደ ዝርግ ቅርፅ ቅርፅም ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ባለ ሶስት አውታረ-መጠን ቅርፅ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

### ሀ. ሰው ሰራሽ/መደበኛ ቅርፆች (Geometric Forms)

ሰው ሰራሽ ቅርፆች የምንላቸው የታወቀ ርዝመት ፣ ቁመት እንዲሁም ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሳጥን ፣ ሲሊንደር ፣ ኮን ፣ ፒራሚድ ፣ እንዲሁም ልዑልን ልንጠቅስ እንችላለን፡፡ ከላይ የጠቀስናቸውን ምሳሌዎች አይነት በየቤታችን ብዙ ቁሳቁሶችን ማግኘት እንችላለን፡፡ ብርጭቆ ፣ ኳስ ፣ የቡና ሲኒ ፣ ቁም ሳጥን ... ወዘተ መደበኛ ቅርፆች በየቤታችን ውስጥ ይገኛሉ፡፡



ምስል 1.9- ሰው ሰራሽ/መደበኛ ቅርጽ



ምስል- 1.10- ሰውሰራሽ/መደበኛ ቅርፆች

## ለ. ተፈጥሯዊ ባለ ሶስት አውታረ-መጠን ቅርፆች (Organic Forms)

ተፈጥሯዊ ባለ ሶስት አውታረ-መጠን ቅርፆች የምንላቸው የታወቀ ርዝመት ፣ ቁመት እንዲሁም ይዘት የሌላቸው ቅጠቢስ ቅርፆች ናቸው፡፡ እነዚህ ቅርፆች በተፈጥሮ የተገኙ ሲሆኑ ስም ልንሰይምላቸው አንችልም፡፡ ከታች በምስሉ ላይ የምንመለከታቸው ቁሳቁሶች ይህን በደንብ ያሳያሉ፡፡




ምስል 1.11- ተፈጥሯዊ ቅርፆች

ባለ ሶስት አውታረ-መጠን ቅርፆችን ቀለም ስትቀቡ በዋናነት የተለየዩ ቀለማትን እንዴት በአንድ ስዕል ውስጥ መጠቀም እንደምትችሉ ማሰብ ይጠበቅባችኋል፡፡


ባለ ሶስት አውታረ መጠን ቅርፃችን ልክ እንደ ባለ ሁለት አውታረ መጠን አንድ አይነት ቀለም ብቻ አንጠቀምም። ምክንያቱም አንድን ሳጥን ቀለም ስንቀባ በተወሰነ መጠን ከላይና ከታች ያለውን የሳጥኑን ክፍል ለመለየት የተለያዩ ቀለማትን ብንቀባ የተሻለ ውበት ይኖረዋል። ለምሳሌ አንድን ሳጥን በወፍራም ወረቀት ሰርተው ከጨረሱ በኋላ የሳጥኑን ሶስት ጎኖች በተለያዩ ቀለማቶች ቀብተው ቢያሳዩ ተማሪዎች የተሻለ የመረዳት እድል ያገኛሉ።

## መልመጃ 1.4

- መምህሩ ከታች ያለውን ሰው ሰራሽ ቅርፅ የተለያዩ ቀለማትን በመቀባት ያሳያሉ። ተማሪዎችም መምህሩ ያሳያቸውን ቅደም ተከተል በመጠቀም የሳጥን ቅርጽ በወረቀት ወይም በካርቶን በመስራት አራት ጎኖችን በተለያዩ ቀለማት በመቀባት አሳዩ



ምስል- 1.12- ቅርፃችን በተለያዩ ቀለማት መለማመድ



ምስል 1.13- ቅርጾችን በተለያዩ ቀለማት ማጥናት

## 1.3. ምጥን ተውኔቶችን መረዳት

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት ስለተመለከታችሁት አጭር ድራማ ወይም ተውኔት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ

ምጥን ተውኔት በትውን ጥበብ ውስጥ የሚመደብ የተውኔት አይነት ነው፡ ፡ የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ ለመኖር ሲል የተለያዩ ክንዋኔዎችን ይተውናሉ፡፡ በዚህም መሠረት የተለያዩ የተፃፉ ወይም ያልተፃፉ ክንውኖችን እጥር ምጥን ያሉ ታሪኮችን በመምረጥ ለእይታ እንዲቀርቡ ማድረግ ነው፡ ፡ ይህ የተውኔት አሰራር መንገድ ምጥን ተውኔት ይባላል፡፡ ምጥን ተውኔት አጭር ግልፅ በሁሉም መንገድ የተመጠነ ሲሆን እንደ ተውኔቱ አይነት ፅሑፈ-ተውኔት (ድርሰት) ሊኖረውም ሆነ ላይኖረውም ይችላል፡፡ ምጥን ተውኔት ከድንገቴ ፈጠራ ተውኔት ጋር ይቀራረባል ወይም ይወራረሳል፡፡

ድንገቴ ፈጠራ ያልተጻፈ ነገር ግን ተራኪው/ተዋናዩ ታሪክ በመፍጠር ምንም አይነት ጽሁፈ-ተውኔት (ድርሰት) ሳይኖር የድርጊቱን ቀደም ተከተል በመከተል ገጸ ባህርያትን በመከፋፈል ተዋንያኑ ቃላት ከራሳቸው ስሜት ጋር በማቀናጀት የሚተወን የተውኔት አይነት ነው፡፡ ምጥን ተውኔት ከድንገቴ ፈጠራ የሚለየው ቃለ-ንግግር (ቃለ-ተውኔት) ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህም ገፀ-ባህርትን በመከፋፈል በተፃፈው ቃለ ንግግር መሠረት ስሜቶችን በመቀያየር መድረክ ላይ የሚቀርብ ነው፡፡ በአጠቃላይ ምጥን ተውኔት የተመጠነ አጠር ያለ ግልፅ ታሪክ ያለው የተውኔት ዓይነት ነው፡፡

### መልመጃ 1.5

- ከሁለት እስከ አምስት ገጽ ያላቸውን ተውኔቶች በመምረጥ በክፍል ውስጥ ሰርታችሁ ለጓደኞቻችሁ አሳዩ

## 1.4. የቁምና አግዳሚ ፎቶግራፍ አነሳስ አይነቶችን መረዳት

### መግቢያ

ፎቶ ግራፍ የአንድን ሰው ፣ እንስሳ ወይም የተፈጥሮ መልከዓ-ምድር ወደ ምስል በመቀየር ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ታሳቢ በማድረግ የተሰራ ነው፡፡ ፎቶ

አንድን ቅጽበታዊ ነገር ባለበት እንድናስታውሰው የሚያደርግ ፈጠራ ነው:: የድሮ ፎቶዎች በጥቁር እና ነጭ ቀለማት ብቻ የሚነሱ ሲሆን የአሁን ጊዜ ፎቶዎች ደግሞ ብዙ ቀለማት ያላቸው ናቸው::

## ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

### ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ከጨረሱ በኋላ

- የተለያዩ አይነት የፎቶ አነሳስ አይነቶችን ለይተው ያውቃሉ
- መሰረታዊ የፎቶግራፍ አላባውያንን ይረዳሉ
- ስለፎቶግራፍ መሰረታዊ ነገሮች ይረዳሉ
- የፎቶግራፍ አላባውያንን በደንብ ይገነዘባሉ
- ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ከጨረሱ በኋላ የተለያዩ ፎቶዎችን በመመልከት መልዕክቶቻቸውን ይረዳሉ
- ፎቶዎችን በመመልከት በአካባቢያቸው የሚገኙ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችን ምን እንደሚመስሉ ይረዳሉ

## የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት ፎቶ ተነስታችሁ ታውቃላችሁ? መቼ እና የት ፎቶ እንደተነሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ

ስለ ፎቶግራፍ አነሳስና አይነቶች ከማንሳታችን በፊት ተማሪዎች ስለ የፎቶግራፍ ማንሻ ካሜራ መቼ እና እንዴት እንደተጀመረ ማስተማር ይገባናል:: ምክንያቱም ከፎቶግራፍ ታሪክ በፊት የካሜራ መገኘት ስለሚቀድም ነው:: በአለም ላይ የመጀመሪያው ካሜራ የተፈጠረው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1816 በኒስፎሪ ኒፕሲ አማካኝነት እንደሆነ ይታመናል:: በፎቶግራፍ ታሪክ ረጅም ዘመን ያስቆጠረው በኒስፎሪ ኒፕሲ አማካኝነት የተነሳው ፎቶ እንደሆነ ይታወቃል:: እስካሁን ባለው መረጃ መሠረት ረጅም ዘመን ያስቆጠረው ፎቶግራፍ እንደሆነ የተለያዩ መዛግብት ላይ ተፅፎ ይገኛል:: የመጀመሪያው ካሜራ የሳጥን ቅርጽ የነበረው ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን እጅግ ብዙ አይነት ካሜራዎች በተለያየ መጠን እና ቅርጽ ተሻሽሎ ይገኛል:: በዋናነት የካሜራ ጥቅም ምስሎችን በፎቶግራ ምስል መልክ ማስቀረት እና ወደ ወረቀት በህትመት መልክ መቀየር ነው::



ምስል 1.14- ጥንታዊ ፎቶ ማንሻ ካሜራ ቅርጽ

በኢትዮጵያም ለመጀመሪያ ጊዜ የፎቶግራፍ ማንሻ ካሜራ ወደ ሃገራችን የገባው በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት በ 1875 ዓ.ም እንደሆነ የታሪክ መዛግብት ያሳያሉ። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ፎቶ የተነሳው ግንቦት 13 ቀን 1875 ዓ.ም አጼ ምኒልክ ነው። ከዚያ በኋላ የቤተ-መንግስት ፎቶ ግራፍ አንሺ የነበረው ቦያጂያን በ1897 ዓ.ም የመጀመሪያውን የህዝብ ፎቶ ቤት በአዲስ አበባ በመክፈት ፎቶን ለህዝብ አስተዋውቋል።

## 1.4.1. መሰረታዊ የፎቶግራፍ አላባውያን

### የማነቃቂያ ጥያቄ


- ፎቶ ግራፍ የሚያነሳ ሰው ምን አይነት እንቅስቃሴዎችን እንደሚያሳይ ተማሪዎች እንዲወያዩ ያድርጓቸው።

በመጀመሪያ ደረጃ ካሜራ ይዘን ፎቶግራፍ ከማንሳታችን ወይም ለተማሪዎች ከማስተማራችን በፊት ለመንሳት የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነጥቦችን ማወቅ ያስፈልጋል። የፎቶግራፍ መሰረታዊ ነገሮች የምንላቸው ብዙ ቢሆኑም በዋናነት ግን ብርሃን ፣ ቀለም ፣ እንቅስቃሴ እና ንድፈ ሃሳብ መሰረታዊ ነገሮች ናቸው።

## ሀ. ብርሃን (Light)

ብርሀን የፎቶግራፍ መሰረታዊ ነገሮች ከሚባሉት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ይይዛል:: ብርሃንን ከተፈጥሮና ሰውሰራሽ መንገድ እናገኛለን:: ሆኖም ከተቻለ የተፈጥሮ ብርሃንን መጠቀም ትክክለኛ የብርሃን እና ተፈጥሯዊ ቀለሞችን ለማግኘት ተመራጭ ነው:: ለዚህም ጠዋት ፀሀይ ከወጣችበት ሰዓት ጀንሮ እስከ አራት ሰዓት ተኩል ድረስ ያለው ጊዜ ለፎቶ ተስማሚ ነው:: በቂ ብርሀን በሌለበት ቦታ ጥሩ ፎት ማንሳት አንችልም:: አንድን ፎቶግራፍ በተለያዩ የብርሃን አይነቶች ልናነሳ እንችላለን:: ለምሳሌ በጥዋትና ማታ የብርሀን አይነቶች (ፀሃይ በምትወጣበት እና በምትገባበት ጊዜ) በእኩለ ቀን እንዲሁም በጨረቃ ብርሃን ፎቶ ማንሳት እንችላለን:: ሆኖም ግን የቀንም ሆነ የማታ ብርሃን የተመጠነ እና በቂ መሆን አለበት::

ለምሳሌ ከታች በምስሉ ላይ እንደምንመለከተው በእንቁላሉ ላይ ያረፈው ብርሃን እና ብርሃኑ የመጣበት አቅጣጫ የእንቁላሉን አካል ሁለት እኩል ቦታ በመክፈሉ ፎቶው የበለጠ ውበት እንዲኖረው አድርጓል::



ምስል 1.15 ጥላ እና ብርሃን

## መልመጃ 1.6

◆ ከታች በምስሉ ላይ የምታዩትን ፎቶግራፍ በመመልከት ስለ ጥላ እና ብርሃን ተናገሩ



ምስል-1.16 የአፕል ፎቶግራፍ

## ለ. ቀለም (Color)

ቀለም የአንድን ፎቶግራፍ ውበት እጅግ ጎልቶ እንዲወጣ ከሚያደርጉ ነገሮች ዋነኛው ነው:: አንድ ፎቶ ግራፍ ውስጥ ቀለማትን ስንጠቀም ስሜትን በቀላሉ ለመግለጽ ፣ ትኩረትን ለመሳብ እና ውበትን ለመጨመር ያግዛል:: ፎቶ ውስጥ የቀለማት ምርጫችን የበለጠ ትኩረት እንዲያገኝ ያግዘዋል:: ለምሳሌ ፎቶ ቤት ሄደን ፎቶ ብንነሳና ፎቷችን ጎልቶ እንዲታይ ከፈለግን የልብሳችን ቀለም እና የግድግዳው ቀለም መመሳሰል የለበትም:: ስለዚህ ቀለማት በፎቶ ውስጥ ብዙ ሚና ይጫወታሉ::

ለምሳሌ ከታች በምስል የሚታየው የዶሮዎች ፎቶ ከአካባቢያቸው ካለው የግድግዳ እና የአረንጓዴ ሳር ቀለም ጋር ህብረት በመፍጠር የዶሮዎቹ ቀለማት የበለጠ ጎልቶ እንዲታይ አድርጎታል ማለት ነው:: የዶሮዎቹ ቀላ ያለ መልክ በደንብ ጎልቶ እንዲታይ ያደረገው ፎቶው የተነሳበት ቦታ ነው:: ስለዚህ ከፊት ለፊት ያለው ምስል ቀለም ደማቅ ሆኖ እንዲታይ ካስፈለገ ከኋላ ያለው ቀለም ደብዛዛ መሆን አለበት



ምስል 1.12- የዶሮ ፎቶግራፍ

## መልመጃ 1.7

- ከታች በምስሉ ላይ በሚታየው ፎቶግራፍ ውስጥ የምትመለከቷቸውን ቀለሞች ተናገሩ



ምስል-1.17 የምሽት ፎቶግራፍ

## ሐ. እንቅስቃሴ (Movement)

እንቅስቃሴ በፎቶግራፍ ውስጥ የተለያዩ እንቅስቃሴ ያላቸውን ነገሮች በፎቶግራፍ ማሳየት ማለት ነው። ለምሳሌ በሰማይ ላይ እየበረረች ያለችን ወፍ ሰማይ ላይ እንዳለች ወይም ክንፏን እንደዘረጋች ፎቶ ብናነሳት እንቀስቃሴ ላይ እንዳለች እንረዳለን ማለት ነው። አንድ ፎቶ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ነገር ብናነሳው ለእይታ

ተጨማሪ ውበት ይኖረዋል ወይም እኛም ፎቶው በምን አይነት ስሜት እንዳለ ለመረዳት እንሞክራለን ማለት ነው፡፡

ምሳሌ፦ ከታች ያለው የጭላዳ ዝንጀሮ ፎቶ በመጓዝ ላይ እያለ የተነሳ ሲሆን ፎቶውን በማየት እንቅስቃሴውን መግለጽ ወይም መረዳት እንችላለን፡፡ ስለዚህ እንቅስቃሴን በፎቶ ለመግለጽ በመሮጥ ላይ ያለን ሰው ፣ በመብረር ላይ ያለችን ወፍ ፣ በአደን ላይ ያለን አንበሳ እንዲሁም በመጋለብ ላይ ያለን ፈረስ በፎቶ እንቅስቃሴን መግለጽ እንችላለን፡፡



ምስል 1.18- በሰሜን ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ የሚገኝ ጭላዳ ዝንጀሮ

## መልመጃ 1.8

- ከታች በምስሉ ላይ የምትመለከቱት  የአትሌት ሀይሌ ገብረ ስላሴ ፎቶ በምን አይነት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳለ ተናገሩ፡፡





ምስል -1.19 የሀይሌ ገብረሥላሴ የፎቶ እንቅስቃሴን ለማሳየት የሚረዳ ምስል

## መ. ንድፈ ሃሳብ (Cmposition)

ንድፈ ሃሳብ የምንለው በአንድ ፎቶግራፍ ውስጥ የሚቀመጡ ነገሮች እንዴት እንደሚደረደሩ ማሰብ ማለት ነው::: ለምሳሌ በአንድ ፎቶ ውስጥ 3 ሰዎች ቢኖሩ እንዴት ሆነው እንደሚቀመጡ ማሰብ ስንጀምር ስለ አወቃቀር እያሰብን ነው ማለት ነው:: ስለዚህ ፎቶው እንዲያምርልን ከመሃል ያለው እንዲቆም ከዳርና ከዳር ያሉት ደግሞ ቢቀመጡ ፎቶው የተሻለ ውበት ይኖረዋል ማለት ነው::

ምሳሌ፡- ከታች በምስሉ እንደምንመለከተው በመጀመሪያው ሰንጠረዥ ፎቶው እንዴት መቀመጥ እንዳለበት የሚያሳይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በመጨረሻ ፎቶው ማስቀመጥ በፈለግንበት ቦታ ላይ ተቀምጦ እናየዋለን:: አንድን የተፈጥሮ ገጽታ ወይም ተራራ በተለያየ አይነት መንገድ ስለን ልናሳየው እንችላለን:: ለዚህም የፀሀይዋን እንቅስቃሴ በመጠቀም የተራራውን እንቅስቃሴ በሚያምር መልኩ ማሳየት እንችላለን::



ምስል 1.20- የንድፈ-ሃሳብ አወቃቀር

አንድን ፎቶግራፍ በደንብ ለመረዳት ከላይ የጠቀስናቸውን መሰረታዊ ሃሳቦችን ማወቅና በሚገባ መተንተን ያስፈልጋል::

### መልመጃ 1.9

- ከታች በምስሉ ላይ የምትመለከቱትን ፎቶግራፍ አወቃቀር እና አቀማመጥ ግለጹ



ምስል 1.21- አወቃቀርን የሚያሳይ ፎቶግራፍ

## 1.4.2. የፎቶግራፍ አነሳስ አይነቶች

ብዙ አይነት የፎቶ ግራፍ አነሳስ አይነቶች ቢኖሩም በዋናነት ግን የቁም (portrait) እና አግዳሚ (landscape) ተብለው ይከፈላሉ::

### ሀ. የቁም (portrait) ፎቶግራፍ አነሳስ

የቁም ፎቶግራፍ አነሳስ አይነት የፎቶው ቁመት ከፎቶው ርዝመት የሚበልጥ ሲሆን ነው:: ይህ የፎቶግራፍ አይነት የሚጠቀመው የሰዎችን ሙሉ አካል እንዲሁም ከደረት በላይ ለማንሳት ፣ የእንሥሣትን መልክ ፣ ረጃጅም ዛፎችን እንዲሁም በፎቶግራፉ ውስጥ ውስን ነገሮችን ብቻ ለማካተት ስንፈልግ ነው:: የቁም ፎቶግራፎችን ስናነሳ በዋናነት የምንመለከተው ከፊት ለፊታችን ያለውን ነገር እንጂ ከጀርባ (background) ያለውን አይደለም:: በዚህም የተነሳ ከፊት ለፊት ያለው ምስል በጣም ጎልቶ እንዲታይ ያግዛል::



ምስል 1.22- የሀመር ሴት ፎቶግራፍ በቁም ፎቶግራፍ አነሳስ ዘዴ

## ለ. አግዳሚ (landscape) ፎቶግራፍ አነሳስ

ይህ የፎቶግራፍ አነሳስ ዘዴ የፎቶው ርዝመት ከፎቶው ቁመት የሚበልጥ ሲሆን በዋናነት የሚጠቅመው በአንድ ፎቶ ውስጥ ብዙ ነገሮችን ለማካተት ነው:: የተፈጥሮን ውብ ገፅታዎች ለማንሳት ፣ ረጃጅም ተራራዎችን አካትተን በምናገኘው ምስል ላይ ሰፊ አድማስ እንዲገኝ የሚመረጥ የፎቶ አነሳስ ዘዴ ነው:: ለምሳሌ ጥቅጥቅ ያለ ደንን ፣ የባህር ዳርቻዎችን ፣ ተራራዎችንና ፏፏቴዎችን ፣ ፀሀይ ስትወጣ እና ስትገባ ያለውን ትዕይንት እንዲሁም ሜዳ ላይ የተሰበሰቡ እንሠሣትን በብዛትና በስፋት ለማካተት የምንጠቀምበት የፎቶግራፍ አነሳስ ዘዴ ነው:: የፀሀይ መግባትን እና መውጣትን ትዕይንት ለማንሳት ስናስብ እጅግ ደማቅ ቀለማትን እና ብዙ ህብረ-ቀለማትን ለማካተት አግዳሚ ፎቶግራፍ ተመራጭ ሆኖ እናገኘዋለን::

### መልመጃ 1.10

◆ ተማሪዎች በተለያዩ መማሪያ መጽሃፍት ውስጥ ያሉትን ፎቶግራፎች የቁም ወይም አግዳሚ የፎቶ አነሳስ አይነቶች መሆናቸውን በቡድን ሆናችሁ በመለየት ተወያዩባቸው

## 1.4.3. ፎቶዎችን በመመልከት መልዕክቶችን መረዳት

ከሺህ ቃል አንድ ስዕል እንዲሉ በአንድ ፎቶ ውስጥ ከሺህ በላይ ቃላትን መግለፅ እንችላለን:: ፎቶዎች የአንድን ማህበረሰብ ባህል ፣ ሃይማኖት ፣ የኑሮ ዘይቤ እንዲሁም የዕለት ከዕለት የኑሮ ሁኔታን ሊገልጹ ይችላሉ:: አንድ ፎቶ በውስጡ አንድና ከዚያ በላይ መልዕክቶችን ሊያስተላልፍ ይችላል:: ፎቶዎች የአንድን ማህበረሰብ ታሪክ ፣ የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም የስልጣኔ ደረጃዎችን ያሳያል:: ለምሳሌ በጉራጌ ዞን የሚገኘውን የጥያ ትክል ድንጋይ ብንመለከት ከብዙ አመታን በፊት በዚያ ቦታ ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን ታሪክ ፣ ባህል ፣ ስልጣኔ እና ሌሎችንም ነገሮች ይገልፃል:: የአንዲት የሀመርን ሴት ፎቶ በመመልከት ምን አይነት ባህል ፣ አኗኗር እና ስልጣኔ ደረጃ ላይ እንደደረሰች በጥቂቱም ቢሆን መናገር እንችላለን:: የወላይታን የጊፋታ በዓል ፣ የጉራጌን መስቀል ፣ የጋሞን ባህላዊ የእርቅ ስርዓት ፣ የኮንሶን የእርከን ስራ... ወዘተ ፎቶግራፎችን በመጠቀም ማሳየት እንችላለን ወይም ከፎቶዎች አይተን መረዳት እንችላለን::

ተማሪዎች አንድን ፎቶ በመመልከት ፅሁፍ ያዘጋጃሉ ፣ ታሪክንና ባህልን ወክለው ትረካዎችን ያዘጋጃሉ ያስረዳሉ ፣ ለውይይት እና ለክርክር የሚሆኑ ሃሳቦችን እንዲነሱ ያደርጋሉ:: ለምሳሌ የጋሞ አባቶች ግጭት ሲፈጠር እንዴት በባህላዊ መንገድ እንደሚያስቆሙት በፎቶ አስደግፈን ብናቀርብና ከፎቶው ተነስተው ተማሪዎች ሙዚቃዊ ፣ ስዕላዊ እንዲሁም ድራማዊ በሆነ መንገድ እንዲያሳዩ ማድረግ ተማሪዎች በአንድ ፎቶ ብዙ ነገር እንዲማሩ ያግዛቸዋል::



ምስል 1.23- የጉራጌን መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ የሚያሳይ ፎቶ

## መልመጃ 1.11

◆ ተማሪዎች በቡድን በመሆን የተለያዩ ፎቶዎችን ከጋዜጣ ላይ በመሰብሰብ ስለ ይዘታቸው ማብራሪያ ይስጡ

## ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ በአካባቢያችን የሚገኙ የተለያዩ ነገሮችን እንዴት መመልከት እንደምንችል አይተናል:: ምልከታ አንድን ነገር ከመስራታችን በፊት ማድረግ ያለብን የሁልጊዜ ተግባር ነው:: ለዚህም የትውን እና የእይታ ጥበባትን ከአካባቢያችን ጋር በማዛመድ የተለያዩ አይነት ጽሁፎችን ፣ ስዕሎችን ፣ መዝሙሮችን እንዲሁም ተውኔቶችን ለመስራት ያግዘናል:: አካባቢያችንን መመልከት ስንጀምር የተፈጥሮን ውበት ማለትም የዛፎችን እንቅስቃሴ ፣ የእንስሳትን ድምጽ ፣ የፏፏቴዎችን ድምጽ ፣ የአበቦችን ቀለማት ለማየትና ለማስመሰል ያግዘናል:: በአጠቃላይ አካባቢያችንን መመልከት ስንጀምር የተለያዩ አይነት ፈጠራዎችን እና ችግር ፈቺ ምርምሮችን በትምህርት ቤታችንም ሆነ በመኖሪያ መንደራችን መስራት እንችላለን ማለት ነው::

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. ድምጽ አልባ ተውኔት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ተማሪዎች የተለያዩ መልዕክት ያላቸውን ፎቶዎች ሰብስባችሁ በማምጣት በክፍል ውስጥ ውድድር አድርጉ
3. በአካባቢያችሁ የሚገኙ በቀላል ስልተ-ምቶች የሚዘመሩ መዝሙሮችን በመለማመድ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ
4. የኖታ እና የእረፍት ምልክቶችን የጊዜ ቆይታ ለማወቅ በእግራችሁ መሬቱን በመምታት ወይም በእጃችሁ በማጨብጨብ እየቆጠራችሁ ተለማመዱ
5. በአካባቢያችሁ የምታውቁትን ሰው በማስመሰል በድምፅ-አልባ ተውኔት እንዴት እንደምትገልፁት ለጓደኞቻችሁ አሳዩ
6. ዝርግ ቅርፆችን እና ቅርፆችን በቤታችሁ ውስጥ ከሚገኙ ቁሳቁሶች ጋር አመሳስሉ

# ምዕራፍ ሁለት

# የግልና የቡድን ትግበራዎች

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች የተለያዩ አይነት የሙዚቃ ምልክቶች ፣ ስታፍን እና ክሌፍን በደንብ ትማራላችሁ:: የተለያዩ የኮላጅ ስዕሎችን ከአካባቢያችሁ በሚገኙ ቁሳቁሶች በመለጣጠፍ ፣ በመገጣጠም ወይም በመቆራረጥ ልዩ ልዩ ስዕሎችን በመስራት ለመምህራችሁ ታሳያላችሁ:: ሀገረሰባዊ ውዝዋዜዎችን እና መዝሙሮችን በግልም ሆነ በቡድን ሆናችሁ በመዘመር ልዩ ተሰጥኦ ያላቸሁ ተማሪዎች በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ልዩ ፕሮግራም ላይ በማቅረብ ችሎታችሁን ታዳብራላችሁ:: ተማሪዎች ሃገረሰባዊ ዜማዎችን ስትለማመዱ አካባቢያችሁንና ባህላችሁን ጠንቅቃችሁ ማወቅ ይገባችኋል:: ድምፅ-አልባ ተውኔቶችን እና ግለ-ተውኔቶችን ወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ መሰረት በማድረግ በግልም ሆነ በቡድን በመለማመድ በጓደኞቻችሁ ፊት እንድታቀርቡ እድሉን ይፈጥርላችኋል::

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ (መስመርና ክፍተቶችን) በመሳልና በማብራራት ቁልፎችንና የሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳን ጽንሰ-ሀሳብ ይረዳሉ

- የቤተሰብ የአብነት እንቅስቃሴዎችን በመዝሙርና በውዝዋዜ ያሳያሉ
- ንድፎችን በመስራት የተለያዩ ቀለማትን መቀባትና በኮላጅ መልክ መለጠፍን ይለማመዳሉ

## 2.1. የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ (ስታፍ) እና ቁልፎች (ክሌፍ)

### መግቢያ

የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ሚባለው አምስት መስመር ያለው እና አራት ክፍት ቦታዎች ያሉት ሲሆን የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳውን በመሳል እና ቁልፎችን በማስቀመጥ የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳን እንገልፃለን፡፡ የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ በዉስጡ በርካታ ነገሮችን የያዘ ቢሆንም በዚህ የ4ኛ የክፍል ደረጃ የምናየው የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ መስመሮች እና ክፍት ቦታዎችን መሳል እና ማብራራት መቻልን ነው፡፡ ሌላኛው ደግሞ በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ ቁልፎችን ማስቀመጥ /መሳል/ እና ኖታዎች የሚቀመጡበትን ቦታ መለየት ይሆናል፡፡

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች ስለ ሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ አሳሳል በሚገባ ይረዳሉ
- በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ የሚቀመጡ የቁልፍ ምልክቶችን ይለያሉ
- በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ የተፃፉ የኖታዎችን ስም በአግባቡ ይለያሉ
- በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ በተቀመጡ የቁልፍ ምልክቶች አማካኝነት የኖታዎች አቀማመጣቸውን ይለያሉ

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ♣ ሙዚቃን በሙዚቃ መሳሪያ የሚጫወቱ ሰዎች እንዴት የሚጫወቱ ይመስላችኋል?


### ሀ. የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ (ስታፍ)

ይህ ከታች የምንመለከተው የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ሲሆን 5 መስመሮች እና 4 ክፍት ቦታዎች አሉት፡፡

ከታች የምንመለከተው የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ የተፃፉት ቁጥሮች

የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ ያሉትን መስመሮችና የክፍት ቦታዎች ከየት ጀምረን እንደምንቆጥራቸው ያሳየናል፡፡ እነዚህን የመስመር ቦታዎች እና ክፍት ቦታዎች የምንቆጥራቸው ከታች ወደ ላይ ነው፡፡


ምሳሌ




ምስል 2.1-የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ መስመሮችና ክፍት ቦታዎች


## የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ ቁልፎችንና ኖታዎችን ማስቀመጥ (መሳል)

ከታች ባለው ምስል ላይ የምንመለከተው በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ ያለው የቁልፍ ምልክት G ቁልፍ ወይም (ትሬብል/ቀጭን ቁልፍ) ብለን የምንጠራውን የቁልፍ አይነት ሲሆን የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳው መስመር ላይ ያሉት ደግሞ የኖታ ስሞች ናቸው፡፡ ከታች ወደ ላይ ሲነበቡ E (ሚ), G (ሶል), B (ሲ) D (ሬ) F (ፋ) በመባል በአለም አቀፍ ደረጃ ተሰይመዋል፡፡





ምስል-2.2 በ G ቁልፍ የስታፍ መስመሮች አሰያየም

በቀጣዩ ምስል ላይ የምንመለከተው የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ (ስታፍ) ክፍት ቦታዎች ላይ ያሉ የኖታ ስሞችን ሲሆን ከታች ወደ ላይ ሲነበቡ F (ፋ) A (ላ) C (ዶ) E (ሚ) በመባል በአለም አቀፍ ደረጃ ይታወቃሉ፡፡





ምስል 2.3- በ G ቁልፍ ስታፍ የክፍት ቦታዎች አሰያየም

ከታች የምትመለከቱት በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ (ስታፍ) ላይ ያለው የቁልፍ ምልክት F ቁልፍ (ቤዝ/ወፍራም ክሌፍ) ብለን የምንጠራው ሲሆን የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ መስመር ላይ ያሉ የኖታ ስሞች ከታች ወደ ላይ ሲነበቡ G (ሶል) B (ሲ) D (ሬ) F(ፋ) A (ላ) በመባል በአለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ ናቸው፡፡




ምስል-2.4 በ F ቁልፍ (ክሌፍ) ስታፍ የመስመሮች አቀማመጥ

ይህ ከታች የምትመለከቱት በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ ያለው የቁልፍ ምልክት F ቁልፍ (ቤዝ/ወፍራም ክሌፍ) ብለን የምንጠራው ሲሆን የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ክፍት ቦታ ላይ ያሉ የኖታ ስሞች በአለም አቀፍ ደረጃ ከታች ወደ ላይ ሲነበቡ A (ላ) C (ዶ) E (ሚ) G (ሶል) በመባል ይጠራሉ፡፡




ምስል 2.5- በ F ቁልፍ (ክሌፍ) ስታፍ የክፍት ቦታዎች አቀማመጥ

## መልመጃ 2.1

- ተማሪዎች የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳን በመሳል፣ ቁልፎችን በማስቀመጥ እና የኖታዎችን ቦታ በመለየት ለመምህራችሁ አሳዩ


## ለ. የሙዚቃ ቁልፎች (ክሌፍ)

ከሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ (ስታፍ) ላይ የምንስላቸው አራት አይነት የሙዚቃ ቁልፎች (ክሌፍ) አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ከላይ የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ እና ቁልፎቹ በሚለው ርዕስ ስር የተመለከትናቸውን ሁለቱን የሙዚቃ ቁልፎች

በዚህ የክፍል ደረጃ እናያለን፡፡


G ቁልፍ (ትሬብል/ቀጭን ክሌፍ) የምንለው አምስት መስመር እና አራት ክፍት ቦታ ያለውን የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ከሳልን በኋላ የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ መነሻውን ቆጥረን ከሁለተኛው መስመር ላይ መነሻ አድርገን እንስለዋለን፡፡ ከመነሻው ተነስተን ስንስለው G ፊደልን የመምሰል ባህሪ ስላለው G ቁልፍ የሚል ስያሜ ሊሰጠው ችሏል፡፡

በምስል 2.6 የምትመለከቱት G ቁልፍ (ትሬብል/ቀጭን ክሌፍ) በመባል ይታወቃል፡፡ (ከጎን የተቀመጠውን የትሬብል ክሌፍ አፃፃፍ ተመልከቱ)



ምስል 2.6 G ቁልፍ (ትሬብል ክሌፍ) ከስታፍ ውጪ እና በስታፍ ላይ

F ቁልፍ (ቤዝ/ወፍራም ክሌፍ) የምንለው አምስት መስመር እና አራት ክፍት ቦታ ያለውን የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ (ስታፍ) ከሳልን በኋላ የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ መነሻውን ቆጥረን ከአራተኛው መስመር ላይ መነሻ አድርገን እንስለዋለን፡፡ በምስል 2.7 የምትመለከቱት F ቁልፍ (ቤዝ/ወፍራም ክሌፍ) በመባል ይታወቃል፡፡ (ከጎን የተቀመጠውን የቤዝ ክሌፍ አፃፃፍ ተመልከቱ)




ምስል 2.7- F ቁልፍ (ቤዝ ክሌፍ) ከስታፍ ውጪ እና በስታፍ ላይ

## ሐ. ረዳት መስመር

ረዳት መስመር ማለት፡- የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ የሙዚቃ ኖታዎችን በምንፅፍበት ወቅት ከሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳው ከላይ እና ከታች ተርፈው

የሚወጡ የሙዚቃ ኖታዎችን የምንፅፍበት ቦታ ነው።


ለምሳሌ፡- ከዚህ በታች የምንመለከተው በ G ቁልፍ (clef) የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ የረዳት መስመሮችን ቦታ ይሆናል።



ምስል 2.8 ኖታ ያልተቀመጠበት ባዶ የረዳት መስመርን የሚያሳየን ምስል


- ከዚህ በታች የምንመለከተው በG ቁልፍ (clef) የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ በረዳት መስመሮች ላይ የምናስቀምጣቸው ኖታዎች እና የኖታ ስሞች ናቸው።

በሙዚቃ መፃፊያ ሠልዳ ላይ ከታች እና ከላይ የሚወጡ ኖታዎች እና የኖታዎች ስሞች




ምስል 2.9 በ G ክሌፍ የረዳት መስመር እና ኖታዎች ስም የሚያሳየን ምስል

ለምሳሌ፡- ከዚህ በታች የምንመለከተው በ F ቁልፍ (clef) የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ የረዳት መስመሮችን ቦታ ይሆናል።




ምስል 2.10 በ F ክሌፍ የረዳት መስመር እና ኖታዎች ስም የሚያሳየን ምስል

## 2.2. ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜዎች

### መግቢያ

በሃገራችን ኢትዮጵያ ብዙ አይነት ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜዎችን እናገኛለን እነዚህን ውዝዋዜዎች በተለያዩ ኩነቶች ልንተገብራችው (ልናያቸው) እንችላለን:: ሃገረሰባዊ ውዝዋዜዎችን ልናይ ከምንችልባቸው ኩነቶች መካከል በሰርግ ፣ በለቅሶ እና በሃገረ-ሰባዊ ክብረበዓላት አከባበር ስነ-ስርዓት ላይ በብዛት ልናገኝ እንችላለን::

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ተማሪዎች፦

- የተለያዩ አካባቢ ያሉትን ሀገረ-ሰባዊ (ባህላዊ) የሰርግ ፣ የለቅሶ ፣ የየአካባቢው ክብረ-በዓላት ውዝዋዜዎችን ከእንቅስቃሴያቸው ጋር ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሳያሉ

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ባህላዊ (አካባቢያዊ) ክብረ በዓላት ላይ በምን በምን ሁኔታ እንደሚከወን ተወያዩ

ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜ ማለት ሀገራዊ የሆነ ወይም የአንድ አካባቢን ባህላዊ ፣ ሀይማኖታዊ እንዲሁም የእለት ከዕለት ተግባራትን በውዝዋዜ/እንቅስቃሴ መግለፅ ማለት ነው:: በየአከባቢው የሚከበሩ ባህላዊ የሆኑ ክብረ-በዓላት ላይ ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜዎችን እናገኛለን:: ሀገረ-ሰባዊ የሰርግ ውዝዋዜ በአንድ አካባቢ በሰርግ ስነ-ስርዓት ላይ የሚታይ ሀገረ-ሰባዊ (ባህላዊ) ውዝዋዜን ያመለክተናል:: ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜ ከሰርግ በተጨማሪ የለቅሶ ውዝዋዜዎችንም ያካትታል:: በአንዳንድ አካባቢ ታዋቂ ሰዎች ፣ የሀገር ሽማግሌዎች ሲሞቱ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ላይ በሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜ እና ጭፈራ ስነ-ስርዓቱ ይከናወናል::

### መልመጃ 2.2

- በአካባቢያችሁ የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊ የሆኑ የሰርግ ፣ የለቅሶ እና የተለያዩ አካባቢዎች ባህላዊ የክብረ በዓላት ውዝዋዜዎችን በመለማመድ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ

## 2.2.1.የቤተሰብ የአብነት እንቅስቃሴዎችን በመዝሙር እና በውዝዋዜ ማሳየት

በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች የቤተሰብ የስራ መዝሙሮችን መጠቀም የተለመደ ነው። ሆኖም ግን አንድ አካባቢ የሚጠቀምበት ግጥም እና መዝሙር ከሌላው አካባቢ በተወሰነ መንገድ እንደየባህሉ ሊለያይ ይችላል። ይህ የትምህርት ርዕስ ተማሪዎች በየአካባቢያቸው ያሉ የቤተሰብ የስራ መዝሙሮችን ከእንቅስቃሴዎቻቸው ጋር እንዲገልፁ ለማድረግ ያግዛል።

በቤት ዉስጥ የሚደረጉ የቤተሰብ እንቅስቃሴዎችን በመዝሙር እና በውዝዋዜ ማሳየት የሚባሉት በቤት ውስጥ የሚደረጉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ለአብነት ያህል ቤት ዉስጥ ስራ በሚሰራበት ወቅት ማለትም ልብስ በማጠብ ፣ ልጅ በማባበል (ማጫወት) ጊዜ ወዘተ መዝሙርን በመዘመር ከውዝዋዜ ጋር መግለፅን ያመለክተናል። ስለዚህ ቤተሰብ ልጆችን ምግብ እንዲበሉላቸው እና ለማስተኛት እንቅስቃሴን በመጠቀም ይዘምራሉ። በአንዳንድ አከባቢዎች በእርሻ ጊዜ እና ሰብል በሚሰበሰብበት ጊዜ የተለያዩ የደቦ መዝሙሮችን ይዘምራሉ።

የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች የምታውቁትን በቤት ውስጥ እና በስራ ቦታ የሚዘወተሩ መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን አስታውሳችሁ ለጓደኞቻችሁ አሰሙ

ምሳሌ- ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ሲንከባከቧቸው ልጆች ስለቤተሰቦቻቸው የሚዘምሩት መዝሙር

### የቤተሰብ ፍቅር

እናቴ በጣም ትወደኛለች
እንጀራ በወጥ ታጎርሰኛለች
አባቴ በጣም ይወደኛል
ክራርና ዋሽንት ይገዛልኛል።




ምስል 2.11- የቤተሰብ ፍቅር መዝሙር በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ

### መልመጃ 2.3

- ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የሚዘመሩትን የቤተሰብ መዝሙሮች በመዘመር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ

## 2.3. ኮላጅን ለስላሳ/ሸካራ በሆኑ አካባቢያዊ ቁሳቁሶች መስራት

### መግቢያ

ኮላጅ ማለት የተለያዩ የወዳደቁ ወይም ከአካቢያችን የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመሰብሰብና በመለጠፍ የሚሰራ የስዕል አይነት ነው:: ኮላጅ አዳዲስ ፈጠራዎችን ባልተለመደ መልኩ የተለያዩ ባህሪያት ያላቸውን (ሸካራ እና ለስላሳ) ቁሳቁሶችን በአንድ ላይ ትርጉም ባለው መልኩ በማሰባጠር ለማቅረብ አይነተኛ መንገድ ነው::

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ

- ከአካባቢያቸው የሚገኙ የወዳደቁ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የኮላጅ ስዕል ይሰራሉ
- የኮላጅ አይነቶችን ለይተው ያውቃሉ

## የማነቃቂያ ጥያቄ

♣ ኮላጅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመምህራችሁ ንገሩ


የኮላጅ ሰዕል በ20ኛው ክፍለ-ዘመን የተጀመረ ሲሆን በዚህ ዘመን ከፍተኛ እድገት ላይ እንደደረሰ መገንዘብ አስፈላጊ ነው:: ኮላጅ ለመስራት ሸካራ/ ለስላሳ ፕላስቲክ ፣ ጨርቅ ፣ አዝርዕቶችን እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶችን እንደ ግብዓት ልንጠቀም እንችላለን:: ከታች በምስሉ ላይ እንደምንመለከተው ተማሪዎች በቤታቸው የሚገኙ ጥራጥሬዎችን በመጠቀም የተለያዩ አበባዎችን ፣ የእንስሳትንና የሰዎችን ምስሎች በቀላል በኮላጅ ስዕል መስራት እንደምትችሉ ለማሳየት ነው:: እንደዚህ አይነት በቀላሉ የሚሰሩ ነገሮችን በመጠቀም በተግባር ስንለማመድ አካባቢያችንን ለማወቅ ፣ የማሰብ እና የመፍጠር ችሎታችንን ለማዳበር ያግዘናል::



ምስል 2.12 የተለያዩ ጥራጥሬዎችን በመጠቀም የተሰራ የነብር ስዕል



ምስል 2.13- የተለያዩ ጥራጥሬዎችን በመጠቀም የተሰራ የወፍ ስዕል



ምስል 1.14- በአዝራር (የልብስ ቁልፍ) ብቻ የተሰራ የኮላጅ ስዕል (ሰዓሊ ምህረቱ ዋሴ)

## 2.3.1.የኮላጅ አይነቶች

ብዙ አይነት የኮላጅ አይነቶች ቢኖሩም በእናንተ ደረጃ ግን ሁለቱን ብቻ

እንመለከታለን፡፡ እነርሱም የወረቀት እና የፎቶ ኮላጅ ናቸው፡፡

## ሀ. የወረቀት ኮላጅ

የወረቀት ኮላጅ የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ወረቀቶች በመቆራረጥ እና በመለጠፍ የተለያዩ እንስሳቶችን ፣ የሰዎችን መልክ ፣ የተፈጥሮን ገፅታ እና ልዩ ልዩ ፈጠራዎችን መስራት እንችላለን፡፡ የዚህ አይነቱ የኮላጅ አሰራር የተጀመረው በስፔናዊው ሰዓሊ ፓብሎ ፒካሶ ነበር፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ የወረቀት አይነቶችን በመሰብሰብ በተዘጋጀው የመለጠፊያ ወፍራም ወረቀት ፣ ካርቶን/ክርታስ ወይም ጠፍጣፋ ጣውላ ላይ በአካባቢያችን በሚገኝ ሙጫ ወይም ኮላ ማጣበቅ እንችላለን፡፡ የኮላጅ ስዕል የማገናዘብና የመፍጠር ችሎታችንን ስለሚያሳድግ በሰራነው ስዕል የተሻለ የእርካታ አቅምን ይፈጥርልናል፡፡ ኮላጅ በባህሪው ብዙ ንክኪ የበዛበት ስለሆነ የማሰብ ፣ አዲስ ነገር የመፍጠር እንዲሁም አንድን ነገር በብዙ አቅጣጫ ለመሞከር እድል ይፈጥርልናል፡፡



ምስል 2.15. የወረቀት ኮላጅ

## ለ. ፎቶ ኮላጅ

ፎቶ ኮላጅ የምንለው የተለያዩ አይነት ፎቶዎችን በመሰብሰብ የምንፈልገውን ሌላ አይነት ስዕል መስራት ነው፡፡ ፎቶዎች የሰዎች ፣ የእንሥሣት እንዲሁም ተፈጥሮአዊ ገፅታን እንዲሁም የተለያዩ ነገሮችን የሚያሳዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ አይነቱ የኮላጅ አሰራር መሰረት የተለያዩ አይነት ፎቶዎችን በመሰብሰብ አዲስ ስዕል መስራት እንችላለን፡፡ የፎቶ ኮላጅ አስቂኝ ነገሮችን ወይም አሻንጉሊት መሰል ስዕሎችን ለመስራት ይጠቅማል፡፡ በዚህም መሰረት ለህፃናት አስቂኝ የሆኑ ስዕሎችን በቀላሉ ከተለያዩ ፎቶዎች በመቆራረጥና በመገጣጠም

መስራት እንችላለን::



ምስል 2.16- አስቂኝ ፎቶ ኮላጅ



ምስል 2.17- ፎቶ ኮላጅ



ምስል 2.18- የወረቀት ኮላጅ


## ምሳሌ 2.1- የወረቀት ኮላጅ ለመስራት የምትከተሉት ቅደም ተከተል

- በመጀመሪያ መቼ እና እንዴት መስራት እንዳለባችሁ ወስኑ
- በኮላጅ የምትስልሉትን ስዕል ወስኑ
- መስራት የምትፈልጉትን ስዕል የምትለጥፉበት ወረቀት/ጣውላ ላይ በትክክል በእርሳስ ንደፉ
- በመቀጠል ንድፉን ተከትላችሁ የተለያዩ ቅለማት ያላቸውን ወረቀቶች በመቆራረጥ አጣብቁ
- በመጨረሻም እስኪደርቅ በመጠበቅ የምትፈልጉት ቦታ ላይ ሰቅላችሁ አስቀምጡ

ጀበና በኮላጅ የስዕል አሰራር ለመስራት በቅደም ተከተል እንደሚከተለው እንመለከታለን።

### መጀመሪያ


በመጀመሪያ ደረጃ የጀበናውን ንድፍ በመለጠፍያ ወረቀቱ ላይ እንነድፈዋለን



ምስል 2.19 የመጀመሪያ ንድፍ

## ሁለተኛ

በሁለተኛ ደረጃ የምንለጥፋቸውን የተለያዩ አይነት ቀለማት ያላቸውን ወረቀቶችን መሰብሰብ



ምስል 2.20 የመጀመሪያው ንድፍ ላይ የሚለጠፉ ባለቀለም ወረቀቶች

## ሶስተኛ

በስዕሉ መሰረት የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ወረቀቶች በማጣበቂያ እናጣብቃለን



ምስል 2.21 ንድፉን በመከተል ወረቀቶችን መለጠፍ መጀመር

## አራተኛ

የጀበናውን አካል ሙሉ በሙሉ በትክክል በቁርጥራጭ ወረቀቶች ማልበስ




ምስል 2.22 የጀበናውን አካል በቁርጥርጭ ወረቀቶች መሸፈን

## አምስተኛ

ከጀርባ ያለውን ባዶ ቦታ በነጭ ጋዜጣ ወይም ወረቀት መሸፈን




ምስል 2.23 ከስዕሉ ጀርባ ያለውን ባዶ ቦታ በተለያዩ ወረቀቶች መሸፈን

## በመጨረሻ

በመጨረሻም ስዕሉ እና ባዶ ቦታው ከተሸፈነ በኋላ በዚህ መልክ የኮላጅ ስዕል አሰራርን በመከተል ጀበና ሰራን ማለት ነው:: ከጨረስን በኋላ ርጥበት ከነካው ወረቀቶቹ ስለሚበሰብሱ እና ስዕሉ ሊበላሽ ስለሚችል ደረቅ በሆነ ቦታ ላይ ሰቅለን እናስቀምጠዋለን::



ምስል 2.24- የመጨረሻው ወረቀት ኮላጅ ስዕል

### መልመጃ 2.4

◆ ከላይ የሰራነውን ኮላጅ መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የምትፈልጉትን የኮላጅ ስዕል በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ

## 2.4. ቅርፆች ፣ ለስላሳነትና ሸካራነት

### መግቢያ

ለስላሳነት ወይም ሸካራነት በአንድ እቃ ላይ ሊኖር የሚችል ሲሆን በማየት ወይም በመዳሰስ ልንረዳው እንችላለን:: በስዕል ውስጥ ሸካራ ወይም ለስላሳ የቁሳቁስ ባህሪ ሲሆን እውነተኛ እና ተፈጥሮአዊ ባህሪን ለመግለጽ እንጠቀምበታለን:: በተያያዘም አንድን ነገር ሸካራነው ስንል ጥንካሬን ፣ በቀላሉ የማይሰበር እና

የጽናት ተምሳሌት መሆኑን ለማሳየት እንጠቀምበታለን። በተቃራኒው ደግሞ ለስላሳ ነገሮችን ቶሎ የሚሰበሩና ጥንቃቄ የሚፈልጉ ነገሮችን እንወክልበታለን።

## ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

**ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች**

- ለስላሳ እና ሸካራ ባህሪያት ያላቸውን እቃዎች ለይተው ያውቃሉ
- የለስላሳ እና ሸካራ አይነቶችን ለይተው ያውቃሉ

## የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን በመንካት እንዲሁም በማየት ለስላሳ እና ሸካራ መሆናቸውን ተናገሩ

## 2.4.1.ለስላሳነትና ሸካራነት

ብዙ አይነት የልስላሴ እና የሻካራነት አይነቶች ቢኖሩም በዚህ የ4ኛ ክፍል ደረጃ ሁለት አይነት የለስላሳና ሻካራ አይነቶችን ልንመለከት እንችላለን።



ምስል 2.25- በእይታ በቻ የምንረዳው ሸካራነትን የሚገልፅ የተጠቀለለ ገመድ

### ሀ. በእይታ ብቻ የምንለየው ሸካራነት ወይም ለስላሳነት (Visual texture)

ይህ የልስላሴ ወይም የሸካራነት አይነት በአይናችን ብቻ በመመልከት

የምንለየውና ምን አይነት ባህሪ እንዳለው ልንናገርለት የምንችለው ነው። ለምሳሌ የተከመረን የድንጋይ ኮረት ፣ የአሸዋ መንገድን ፣ ልሙጥ መስታወትን ወይም የመኪና ጎማን በሩቅ (በእጃችን ሳንነካ) በአይናችን ብቻ በማየት ምን አይነት ባህሪ እንዳለው መናገር ከቻልን የእይታ ሸካራነት ወይም ለስላሳነት ብለን እንጠራዋለን። በቤታችን ውስጥ ፣ በትምህርት ቤት ወይም በሠፈራችን የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመመልከት ብቻ ይህ ለስላሳ ነው ወይም ይህ ሸካራ ነው ብለን መናገር ከቻልን በእይታ ብቻ የምንለየው ሸካራነት ወይም ለስላሳነት ተብሎ ይጠራል።

ለምሳሌ ከታች በስዕሉ ላይ የምንመለከተውን የጠጠር ክምር በአይናችን ብቻ በመመልከት ሸካራ መሆኑን ማወቅ እንችላለን።



ምስል 2.26- በመዳሰስ የምንረዳው የሸካራነት አይነት የጠጠር ክምር

## ለ. እውነተኛ ሸካራነት ወይም ለስላሳነት (real texture)

ይህ የልስላሴ ወይም ሸካራነት ባህሪ ደግሞ የእቃውን ምንነት ለመረዳት በእጃችንም ሆነ በሌሎች የሰውነት ክፍሎቻችን በመንካት የምናውቀው ሲሆን ነው። ስለዚህ አንድን እቃ በእጃችን ከዳሰሰን በኋላ የምንገነዘበው የልስላሴ ወይም የሸካራነት ባህሪ እውነተኛ የሸካራ ወይም የልስላሴ ባህሪ ነው። ለምሳሌ ማየት የተሳናቸው የሚያነቡት መፅሃፍ (ብሬል) ነገሮችን የሚረዱት በመዳሰስ ነው።


ለምሳሌ ከታች በምስሉ እንደምንረዳው አንድን የዛፍ ግንድ በእጃችን እየዳሰስን እውነተኛ ባህሪው ሸካራ መሆኑን ልንረዳ እንችላለን።




ምስል 2.27- በእጃችን በመዳሰስ የምንለየው የሸካራ እና ልስላሴ ባህሪ

## ምሳሌ


የተለያየ አይነት ሸካራ ባህሪ ያላቸው ነገሮች ላይ ወረቀት በማስደገፍ በእርሳስ አስደግፈን በመቀባት የተለያዩ አይነት ዲዛይኖችን መስራት እንችላለን። ከነዚህም መካከል ሳንቲሞችን ፣ የወለል ንጣፎችን ፣ የጫማ የውስጥ ሶሎችን እንዲሁም የተለየ ዲዛይን ያላቸውን ነገሮችን መስራት እንችላለን።



ምስል 2.28 ሸካራ ቁሳቁሶችን ወደ ወረቀት ማተም



ምስል 2.29- ሸካራ እቃዎች ወረቀት ላይ ሲታተሙ



ምስል 2.30- ሸካራ ነገሮች በወረቀት ላይ ሲታታሙ

ይህን መሰረት በማድረግ ሌሎች ተጨማሪ ሸካራ የሆኑ ነገሮችን መስራት እንችላለን።



ምስል 2.31- ሳንቲሞችን ወረቀት ላይ በማስደገፍ የተሰራ

መልመጃ 2.5

◆ ተማሪዎች ሸካራ የሆኑ ቁሳቁሶች ላይ በማስደገፍ የተለያዩ ዲዛይኖችን ስሩ

**የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች**

- ወረቀት
- እርሳስ
- ሸካራ ቁስ

## 2.5. ድምፅ-አልባ ተውኔትና ግለ-ተውኔት (መነባንብ)

### መግቢያ

ድምፅ-አልባ ተውኔት እና ግለ ተውኔት በአንድ ሰው ሊሰሩ የሚችሉ የመድረክ ላይ ተውኔቶች ናቸው። ድምፅ-አልባ ተውኔት ያለ ድምጽ በዝምታ የሚተወን ሲሆን ግለ ተውኔት ግን በድምጽ ፣ በዜማ እና በግጥም መልክ የራሳችንን ስሜት በመጨመር መድረክ ላይ የምናቀርበው ነው። ድምፅ-አልባ ተውኔትን በምዕራፍ አንድ ስለተመለከት አሁን ደግሞ ግለ-ተውኔትን (መነባንብን) እንመለከታለን።

## ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

### ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ

- ስለ ግለ ተውኔት በሚገባ ይረዳሉ
- መነባንቦችን መሰረት በማድረግ ግለ ተውኔቶችን ያቀርባሉ
- ለግለ-ተውኔት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ለይተው ያውቃሉ

## የማነቃቂያ ጥያቄ

- ከዚህ በፊት ግጥም አንብባችሁ ታውቃላችሁ? ያነበባችሁትን ግጥም እስኪ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ

ግለ- ተውኔት ከትወና አይነት አንዱ ሲሆን በአንድ ግለሰብ ብቻ የሚሰራ የተውኔት አይነት ነው:: አንድን ታሪክ በአንድ ገፀ-ባህሪ እና በአንድ ተዋናይ ለተመልካች የምናሳይበት የትወና መንገድ ነው:: ግለ-ተውኔት በንግግር መልክ የተፃፈ ግጥም ነው:: ነገር ግን ሲቀርብ ግጥማዊ ይዘቱ እና ዜማው ጠፍቶ በተውኔት መልክ የሚቀርብ ነው:: ተዋናዩ ታሪኩን በመወከል ስሜትን በመጨመር ታሪኩን እውነተኛ ለማስመሰል ይተውናል:: ግለ ተውኔት በሶስት ይከፈላል:: እነርሱም ድራማዊ መነባነብ ፣ ሶሊሎክና የውስጥ መነባነብ ናቸው::



ምስል 2.32- ከመድረክ ላይ የተነሳ ግለ ተውኔት ፎቶ

## 2.5.1.ድራማዊ መነባንብ

በግለሰብ መልክ በአንድ ገፀባህሪ ንግግር የተፃፈ ግጥም ነው:: የታሪኩ ባለቤት ምንነት ፣ ስነ ልቦና እና ስሜትን ከግምት ውስጥ በማስገባት በአንድ ገጸ-ባህሪ ድምፅ አልባ በሆነ መንገድ የሚተወን የተውኔት አይነት ነው:: ይህንን አይነት ግለ-ትወና ለመስራት በመጀመሪያ የታሪኩን መነሻ እና ባህሪ ፣ የራሳችንን ፍላጎት እና ምን አይነት የስሜት መውጣት እና መውረድ እንደሚያስፈልገው በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል:: መምህሩም ተማሪዎችን ግለ ተውኔት እንዲለማመዱ ሲያደርግ በመጀመሪያ ተማሪዎችን ስለ ታሪኩ በሚገባ እንዲያውቁ ማስተማር ይገባዋል:: በመቀጠል ተማሪዎች በሚሰሩት ግለ ተውኔት ውስጥ ምን አይነት ስሜቶች (ለምሳሌ የለቅሶ ፣ የሀዘን ፣ የደስታ ፣ የንዴት ወዘተ) እንደሚያስፈልጉ በደንብ ማወቅ ይጠበቅበታል:: ሁለት የመነባንብ አይነቶች አሉ:: እነርሱም ሶኪሎክ መነባንብ እና የውስጥ መነባንብ ናቸው:: ሶኪሎክ መነባንብ አንድ ገፀ-ባህሪ ሃሳቡን ወይም ስሚቱን ጮክ ብሎ የሚገልጽበት የትወና አይነት ሲሆን የውስጥ መነባንብ ደግሞ በድራማ ውስጥ ገፀ-ባህሪው የራሱን ማንነት ፣ ፍላጎቱን እና በውስጡ ያለውን ስሜት ወይም ጥያቄ ብቻውን ሆኖ የሚተርክበት የግለ-ተውኔት አይነት ነው::

### መልመጃ 2.6

- ተማሪዎች ከዚህ በታች ያለውን መነባንብ የራሳችሁን ስሜት እና እንቅስቃሴ ጨምራችሁበት ለክፍል ተማሪዎች አሳዩ::

እማራለሁ እመራመራለሁ
እማራለሁ እመራመራለሁ
ለኢትዮጵጵያ ክብር እኖራለሁ
የድህነትን ቀንበር እሰብራለሁ
እማራለሁ እመራመራለሁ
እናትና አባቴን ቀና ላደርጋቸው
ጠንክሬ ተምሬ ለታናናሾቼ አርዓያ ልሆናቸው
መምህሩ ሲያስተምር በጥሞና አድምጨ
ያልገባኝን ሁሉ አልገባኝም ብየ ጠይቄ

የተሰጠኝን የክፍል እና የቤት ስራ በጥንቃቄ ሰርቼ
አጥንቼ መጥቼ ፈተናየንም ደፍኜ
እናትና አባቴን ቀና ላደርጋቸው
ጎብዤ ተምሬ ለታናናሾቼ አርዓያ ልሆናቸው
እማራለሁ እኔስ እመራመራለሁ በርትቼ
ተምሬ አጥንቼ ተምሬ አንደኛ እሆናለሁ
ነገ ዶክተር ኢንጅነር አርቲስት ለመሆን
ነገ መምህር ፓይለት ጠቅላይ ሚኒስቴር ለመሆን
ዛሬን እማራለሁ ዛሬን እመራመራለሁ
ጎብዤ ጠንክሬ ተምሬ ካሰብኩበት እደርሳልሁ
ታድያ እኔ እናትና አባቴን ቀና ላደርጋቸው
የድህነትን ቀንበር ለመስበር ተነስቻለሁ
በርትቼ ጎብዤ ተምሬ ልመራመር ዛሬ ቆርጫለሁ
እናንተም እንደኔ ተምራችሁ
አንደኛ መውጣት ከተመኛችሁ
ተማሩ ተመራመሩ ጎብዛችሁ
ካልሆነ ምኞት ሃሳብ ብቻውን
አያደርሰንም ከፍላጎት ድላችን
ነገ ዶክተር መሆን የምንችለው
ዛሬን በርትተን ማጥናት ስንችል ነው
ነገን ኢንጅነር መሆን የምንችለው ስንጎብዝ ነው
ታላላቆቻችንን አክብረን መታዘዝ ስንችል ነው
አለዚያማ አንችም አንተም በሃሳብ ትቀራለህ
ካልጣርሽ ካልበረታሽ በሃሳብ ትቀሪያለች
ስለዚህ ዛሬ ወስኝ ዛሬን ወስን ተነስ
ጎበዝ ጠንክረህ ለአንደኛነት ዛሬ ተነስ
(ግጥም ጸሃፊ- ታምራት አብርሃም)

## 2.5.2. ተውኔቶችን ለተመልካች ማቅረብ

ተማሪዎች የሰሯቸውን ተውኔቶች በተመልካቾች ፊት በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ማቅረብ ለሌላ ተጨማሪ ተውኔት ስለሚያነሳሳ መለመድ ያለበት ተግባር ነው:: ተውኔታችን በቀላሉ ተመልካቾች ፊት እንዲደርስ ተዋንያን ሁልጊዜ ወደ ተመልካቾት ፊታቸውን በማዞር መስራት አለባቸው:: ሁልጊዜ ተመልካቾች ፊታችን ላይ የሚፈጠረውን ስሜት ማየት ስላለባቸው ፊት ለፊት ቆመን ስንተውን በቀላሉ መልዕክቱን የረዱታል:: መድረክ ላይ ወይም በክፍል ውስጥ ለተመልካቾች ጀርባችንን ከሰጠን ማስተላለፍ የፈለግነው ድራማ ፣ ግጥም ወይም መነባንብ ለተመልካች በትክክል ሳይደርስ ይቀራል ማለት ነው::: ሌላኛው ደግሞ ድምፃችን ለሁሉም ተመልካች መሰማት መቻል አለበት:: ቀስ ባለ ድምጽ መድረክ ላይ ካቀረብን ማስተላለፍ የሚገባንን መልዕክት ላናስተላልፍ ስለምንችል ሁልጊዜ ተውኔት ከማቅረባችን በፊት ከፍ ባለ ድምፅ ማቅረብ እንዳለብን ማስታወስ ይገባናል::

በተለይ ድምፅ-አልባ ተውኔቶችን በምናቀርብበት ጊዜ በተውኔቱ መካከል በስህተት ንግግር እንዳናስገባ መጠንቀቅ ይገባል:: ተመልካቾች በተውኔቱ ቢስቁ እንኳን ተዋናዩ በምንም ሁኔታ መሳቅ የለበትም:: መምህሩም ተማሪዎችን ይህንን እንዳያደርጉ በደንብ ማለማመድ እና ማስታወስ ይገባቸዋል:: እነዚህ ነገሮች ከተሟሉ መድረክ ላይ የሚቀርበው ተውኔት በትክክል መልዕክቱ እንዲተላለፍ ይሆናል::

### መልመጃ 2.7

- ተማሪዎችን የተለያዩ በአካባቢያችሁ የሚገኙ ትውፊታዊ ፉከራዎችን ፣ ሽለላዎችን እንዲሁም ቀረርቶዎችን በግጥም ወይም በመነባንብ መልክ አቅርቡ

## ማጠቃለያ

በምዕራፍ ሁለት ስለ ግለ ተውኔቶች (መነባንብ) መድረክ ላይ እንዴት እንደሚቀርብ ተመልክተናል። አንድ ግለ ተውኔት ለተመልካቾች ስናቀርብ የምናሳየው የስሜት እና የሰውነት እንቅስቃሴን ከመነባነቡ ጋር ማዋሃድ እንዳለብን ተመልክተናል። የኮላጅ አሰራር እና የኮላጅ አይነቶችንም እንዲሁ በስፋት ተመልክተናል። ሁለት አይነት የኮላጅ አይነቶችን ተመልክተናል። እነርሱም የወረቀት ኮላጅ እና የፎቶ ኮላጅ ናቸው። ሃገረሰባዊ ውዝዋዜዎችን ከዜማዎች ጋር በማዋሀድ መዝሙሮችን ለመዘመር እንደሚያግዝም ተረድተናል። በሙዚቃ ማፃፊያ ሰሌዳ ላይ የሙዚቃ ቁልፎችን እና ኖታዎችን እንዴት መፃፍ እንደሚቻል በስፋት ለመመልከት ችለናል።

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. የኮላጅ አይነቶችን ዘርዝሩ
2. ተውኔቶችን ለተመልካች ለማቅረብ ምን ያስፈልጋል?
3. ሳንቲሞችን አስደግፋችሁ የተለያዩ ዲዛይኖችን ስሩ
4. ስለ ቤተቦቻችሁ የራሳችሁን ግጥሞች በመጻፍ እና አዲስ ዜማ በመፍጠር መዝሙር ተለማመዱ
5. በኖታ መፃፍያ ሰሌዳ ላይ የተቀመጡ ምልክቶችን በመልከት ዘምሩ

# ምዕራፍ ሦስት

# የትውን እና የእይታ ጥበባት ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጠቀሜታ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የትውን እና እይታ ጥበባት ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታን እንመለከታለን። ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ተውኔት በሁሉም የአለም ጫፍ ሰዎችን ያለ ምንም ቋንቋ ማግባባት የሚችሉ አለምአቀፍ የመግባቢያ ቋንቋዎች ናቸው። የትውን እና የእይታ ጥበባት የአንድን ማህበረሰብ ታሪክ ፣ ባህልና እሴት ለመጠበቅ እንዲሁም ለማስተዋወቅ ትልቅ ሚና አላቸው። አለምን ያለ ስነ- ጥበብ ፣ ያለ ሙዚቃ እንዲሁም ያለ ተውኔት እስኪ እናስባት…? ከጥንት ጀምሮ የሰዎችን ታሪክ ስንመለከት ከሙዚቃ ፣ ከንድፍ ፣ ቅርፃ-ቅርፅ ፣ ቀለም-ቅብ እንዲሁም ድራማዊ እንቅስቃሴዎች ጋር የተቆራኘ ነው። ጥንታዊ የዋሻ ስዕሎች የሰዎችን የቀድሞ አስተሳሰብ የስልጣኔ ደረጃ በስዕል መልክ በማስቀመጥ አሁን ለደረስንበት የመጠቀ ስልጣኔ ደረጃ እንድንደርስ ትልቁን አስተዋጽኦ አበርክቷል።

በዚህ ምዕራፍ ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ትያትር ለማህበረሰቡ የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ለማንሳት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ተማሪዎች ነገሮችን በቀላሉ ስዕላዊ እና ሙዚቃዊ በሆነ መንገድ እንዲረዱ እና የፈጠራ ችሎታቸውን

ለማሳደግ እንዲያግዛቸው ለማድረግ ነው:: የአንድን ማህበረሰብ እድገት ለማፋጠን ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ትልቅ ሚና አለው:: ለዚህም ደግሞ ማህበረሰባዊ ስዕልን (community art) ማሳደግ ያስፈልጋል::

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ታሪካዊ ቦታዎችን ይጎበኛሉ
- አካባቢያዊ ጥበቦችን በመጠቀም መዝሙሮችን ፣ ድምፅ-አልባ ተውኔቶችን ፣ ውዝዋዜዎችንና ግለ-ተውኔቶችን ይከውናሉ
- የሚታወቁ ሀገረሰባዊ መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን ይማራሉ
- ምልክቶችን ፣ የቤተሰቦቻቸውንና የጓደኞቻቸውን የልብስ ቀለማት ፣ የሃገራቸውንና የክልላቸውን የባንዲራ ቀለማት ለይተው ያውቃሉ

# 3.1. የትውን እና የእይታ ጥበባት በማህበረሰቡ ታሪክ እና ባህል ውስጥ ያለው ሚና

## መግቢያ

የትውን እና የእይታ ጥበብ ለአንድ ማህበረሰብ እድገት ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታን ያበረክታል:: የትውን እና የእይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ ባህል እድገት እንዲሁም ታሪክን ጠብቆ ለማቆየትና ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ ትልቅ ሚና አለው:: ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ተውኔት ለአንድ ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ጠቀሜታዎችን እንደሚከተለው እንመለከታለን::

## ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ትያትር የሚያበረክተውን ሚና ያውቃሉ
- የትውን እና የእይታ ጥበባት የማህበረሰቡን ታሪክ እና ባህል ከመጠበቅ አንፃር የሚያበረክተውን ጠቀሜታ በሚገባ ይረዳሉ
- ስነ-ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያውቃሉ
- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ሃገረሰባዊ ጥበቦችን እና ታሪካዊ ቅርሶችን

ብሎም ባህሎችን ያውቃሉ

- ስነ ጥበብ ለአንድ ማህበረሰብ የባህል እድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ያውቃሉ

## የማነቃቂያ ተግባራት

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ባህላዊ እና ታሪካዊ የሆኑ እሴቶችን በምን አይነት ሁኔታ እንደምትገልጹ ተናገሩ/ አሳዩ
- ከዚህ በፊት በአካባቢያችሁ የምታውቁት ሰዓሊ እና ስዕል በመሸጥ የሚታወቅ ባለሞያ ካለ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

## 3.1.1.የእይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው ጠቀሜታ

በዚህ ርዕስ የእይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተውን ታሪካዊ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች በስፋት እንመለከታለን::

### ሀ. ስነ ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ

ስነ ጥበብ ባህልንና እሴትን ከማስተዋወቅ በተጨማሪ የገንዘብ ምንጭ ይሆናል:: በየአካባቢያችን ያሉትን ቤተ-መዘክሮችን ፣ የባህል ማዕከሎችን እንዲሁም የስዕል መሳያ ቦታዎችን ብናስፋፋ ከሚፈጠረው የስራ እድል በተጨማሪ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሃገር ዜጎች መጥተው ሊያዩ ፣ ሊገዙ እንዲሁም ሊዝናኑበት ይችላሉ::



ምስል 3.1- የስዕል መሸጫ ሱቅ/ጋለሪ

ለምሳሌ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የጋሞ የባህል ማዕከል ፣ የኮንሶ ህዝቦች ሙዝየም ፣ የዎላይታ ጉታራ የባህል ማዕከል ፣ የጉራጌ ባህል ማዕከል … ወዘተ ባህልን ከማስተዋወቅ ባሻገር ለገንዘብ ማስገኛ ከፍተኛ የቱሪዝም ምንጭ እንዲሆኑ በደንብ ማስተዋወቅ እና መስራት ይቻላል::

አንድ ማህበረሰብ የአከባቢዉን ሙዚቃ ለማህበረሰቡ በሚያቀርብበት ወቅት የተለያዩ አካባቢያዊ ታሪኮችን ፣ አካባቢያዊ ምርቶችን ፣ አካባቢያዊ አልባሳትን ፣ አካባቢያዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን እና የተለያዩ አካባቢያዊ ቁሶችን ለተለያየ ማህበረሰብ በማስተዋወቅ ሙዚቃ ትልቁን ሚና ይጫወታል::

መልመጃ 3.1

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቤተ መዘክሮች ወይም የባህል ማዕከሎች ካሉ በውስጡ ስላሉ ቅርሶች ወይም ስዕሎች ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ

## ለ. ስነ ጥበብ የማህበረሰቡን ባህል እና እሴት ከመጠበቅ አንፃር የሚያበረክተው ጠቀሜታ

እንደ ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ብዝሀነትን በአንድ ክልል እንደሚያስተናግድ ማህበረሰብ ሰዎች ባህላቸውንና ማንነታቸውን ለማሳየት ስነ ጥበብ ጉልህ አስተዋፃኦ አለው:: ስነ-ጥበብ በቡድንም ሆነ በግል ውበትን ጎልቶ እንዲወጣ ያግዛል:: ለምሳሌ ሴቶች በጋብቻ ወቅት አምሮባቸው እንዲታዩ ከሚለብሱት ልብስ ጀምሮ እንደየባህላቸው ለመዋቢያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ:: ይህም ማለት የቀለማት ምርጫዎቻችን ፣ የልብስ ዲዛይኖቻችን እንዲሁም የምንጠቀምባቸው ጌጣጌጦች ሁሉ በእያንዳንዳችን ባህል ውስጥ የምናከናውናቸው የዕለት ከዕለት ተግባሮቻችን ናቸው:: ቀለማት ባህላችንን ስለሚያንጸባርቁ እያንዳንዱ ብሄረሰብ የራሱ የሚወደውና የሚወክለውን ቀለም እንደ መገለጫ አድርጎ በልብስ መልክ ፣ በባንዲራ እና በቤት ውስጥ በሚገኙ ቁሳቁሶች ላይ ሊጠቀም ይችላል:: ለዚህ ደግሞ የጋሞን ድንጉዛ ፣ የጉራጌን ቀሚስ ፣ የአሪ ብሄረሰብን ልብስ ፣ የኮይሻ ቀሚስ… ወዘተ የራሳቸውን ቀለም እና ዲዛይኖች እንዴት እንደሚጠቀሙበት ማየት እንችላለን:: ከዚህም በተጨማሪ የቤት አሰራር ጥበቦቻችን ፣ የሸክላ ስራዎቻችን ፣ የሽመና እና የብረታብረት ስራዎቻችንን የምንሰራበት መንገድ የውበትን ጽንሰ-ሃሳብ የምንረዳበት መንገድ እንደ ባህላችን የሚለያይ ነው::

መምህሩ ከላይ የተጠቀሱትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ስነ ጥበብ በባህል ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ ተማሪዎች በቡደን ሆነው እንዲወያዩ ማድረግ አስፈላጊ ነው::

መልመጃ 3.2

- ተማሪዎች በቡድን በቡድን በመሆን ከአካባቢያችሁ ባህል ውጭ የምታውቁትን የሌሎች ማህበረሰቦችን የአለባበስ ፣ የአመጋገብ እና የአኗኗር ሁኔታ አሳዩ/ተናገሩ::

## ሐ. ሃገረሰባዊ እውቀትን እና ስልጣኔን ለማዳበር

ስነ ጥበብ ውስጣዊ ስሜታችንን አውጥተን እንድናሳይ ስለሚያግዘን በጋራ የመስራት እና ማህበራዊ መሰረቶቻችንን ያጠናክራል:: በማህበረሰባችን ውስጥ የሚገኙ እውቀቶችን በማውጣት የመናገር ፣ የማስታዎስ እና የመፍጠር ችሎታችንን ለማዳበር ትልቅ አስተዋጽኦ አለው:: ትውፊታዊ ስዕሎችን የሚሰሩ ሰዓሊያንንም ለማበረታት ያግዛል:: ትውፊታዊ ስዕሎችን የሚስሉ ስንል በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በትምህርት ሳይሆን በራሳቸው ጥረት ያገኙትን እውቀት የማህበረሰቡን እሴት እና እውነተኛ ባህላዊ በሆነ መንገድ የሚስሉትን ለማበረታታት ያግዛል:: በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖሩትን የአካል ጉዳተኞችን ተሳታፊ ለማድረግ ስነ ጥበብ ትልቅ አስተዋፆ አለው:: ለምሳሌ መናገር እና መስማት የማይችል ሰው ሃሳቡን በስዕል ሊገልጽ ይችላል:: መስማት የማይችል በስዕል ፣ ማየት የማይችል በሙዚቃ ወይም በምልክት ፣ መናገርም ሆነ መስማት የማይችልን ሰው ደግሞ በንክኪ ነገሮችን እንዲገነዘብ ለማድረግ የትውን እና እይታ ጥበባት ትልቅ ሚና አላቸው::

ቀደምት ሃገረሰባዊ ስልጣኔዎችን ለማስታወስ ስነ-ጥበብ ጉልህ ድርሻ አለው:: በኢትዮጵያ የነበሩ ትልልቅ ስልጣኔዎችን ለአሁኑ ትውልድ ለማስተላለፍ ቀዳሚ ነው:: ቅርፃ ቅርፅ ፣ ቀለም ቅብ እንዲሁም የንድፍ ስራዎች ቀደምት ስልጣኔዎችን በሰፊው ያሳዩናል:: ከስዕሎቹ በመነሳት ድርሰት መጻፍ ፣ የተለያዩ ሙዚቃዊ ድርሰቶችን መስራት እንዲሁም ተውኔት ማቅረብ እንችላለን ማለት ነው::

ስነ ጥበብ ባህልን ለማስተዋወቅ ጉልህ ሚና አለው:: ለምሳሌ በደቡብ ኦሞ የሚገኙ የተለያዩ ብሄረሰቦች ማለትም የሀመር ፣ ሙርሲ ፣ በና ፣ ኛንጋቶም

እና የአሪ ብሄረሰቦች የራሳቸው የሆነ ሃገረሰባዊ የመዋቢያ እና የጌጣጌጥ መጠቀሚያዎች አላቸው:: ወንዶችና ሴቶች ሰውነታቸው ላይ የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን የአፈር አይነቶች በጥብጠው በመቀባት ባህላዊ ውዝዋዜዎችን በቡድን ሆነው ሲጨፍሩ እጅግ ውብ ድምቀትን ይፈጥራሉ:: ወዝዋዜዎቻቸውም በሙዚቃ ፤ በስዕል እንዲሁም ድራማዊ በሆነ መንገድ ስለሚቀርብ ባህልን ከማስተዋወቅ ጎን ለጎን ለገቢ ምንጭ በመሆን ያገለግላል::



ምስል 3.2 የሙርሲ ብሄረሰብ ስዕል (ሠዓሊ ምህረቱ ዋሴ)

ፎቶ የቅርብንም ሆነ የሩቅ ጊዜን በተጨባጭ መረጃዎች ለማስደገፍ ስለሚያግዝ ቦታን ፤ ጊዜን እንዲሁም ሁኒታዎችን ለማስታወስ አይነተኛ መንገድ ነው:: ለምሳሌ በጋሞ ባህል መሰረት ግጭት በተፈጠረ ሰዓት ለማስቆም እርጥብ ሳር ወይም ጨፌ ይዞ ከፊት ከቆመ በሁለቱም ወገን ግጭቱን ወድያውኑ ያቆማሉ:: ከታች ያሉት ፎቶዎችን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በክርክር ፤ በድራማ ወይም በሙዚቃ መልኩ ሊገልጿቸው ይችላሉ::



ምስል 3.3 - የጋሞ ሽማግሌዎች የግጭት አፈታት ስርዓትን የሚያሳይ ፎቶ

## መልመጃ 3.3

◆ ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የሚገኙ ሰዓሊዎች የተለያዩ ቀለሞችን እንዴት እንደሚያዘጋጁ በመጠየቅ ሰርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## መ. ታሪካዊ ቅርሶችን መጎብኘት

ታሪክን ለመገንዘብ ስነ-ጥበብ አይነተኛ መንገድ ነው፡፡ ከዛሬ አምስት መቶ አመት በፊት ስለነበረው የሰው ልጆች ታሪክና የአኗኗር ሁኔታ ለመገንዘብ በስዕል ፣ በፎቶ እንዲሁም በቅርፃ ቅርፅ መልክ የተቀመጡ ነገሮችን እንደ ትልቅ ማስረጃ ልንወስዳቸው እንችላለን፡፡ ከፎቶዎቹ በመነሳትም የሰዎችን የኑሮ እንዲሁም የስልጣኔ ደረጃዎችን መገንዘብ እንችላለን፡፡ ታሪካዊ ቅርሶችን መጎብኘት በአካባቢያችን ያሉትን ነገሮች እንድናውቅ እድሉን ይሰጠናል፡፡ ለምሳሌ የጥያን ትክል ድንጋይ ስንመለከት የጥንት ሰዎች ምን አይነት ስራ እንደሰሩ በድንጋይ ላይ ጽፈው አስቀምጠዋል፡፡ የጥያ ትክል ድንጋይ መካነ መቃብር ላይ ለመታሰቢያነት የሚቆም ሲሆን ድንጋዩ ላይ የተለያዩ ምልክቶች ፣ የሰዎች ምስሎች ፣ ጎራዴ እና ልዩ ልዩ የሆኑ ጌጣጌጦች ተስለውበት ማየት እንችላለን፡፡

የኮንሶ ባህላዊ ቅርፃ-ቅርፅን (ዋካን) ስንመለከት በኮንሶ ባህል ለጎሳ መሪዎች እና ለጀግና ቤተሰቦች  የሰዎችን ምስል በእንጨት በመስራት መቃብራቸው ላይ ወይም የቤታቸው በር አካባቢ በማቆም ለማስታወሻ እንዲሆን ይተከላል፡፡ ቅርፆችም የእናት፣ የአባት እና የልጆችም ምስል በጋራ አንድ ወጥ ከሆነ ወፍራም እንጨጥ ተጠርቦ ይዘጋጃል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የተለያዩ አካባቢዎችን ስትጎበኙ የሌላውን ማህበረሰብ ባህል እና ታሪካቸውን ምን እንደሚመስል ልትገነዘቡ ይገባል፡፡



ምስል 3.4- የኮንሶ የእንጨት ቅርጽ ዋካ

## መልመጃ 3.4

ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የሚገኙ ታሪካዊ እና ባህላዊ ነገሮችን በመጎብኘት ወይም ሰዎችን በመጠየቅ ስላያችሁት እና ስለሰማችሁት ነገር ጽፋችሁ ወይም ስላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።

## ሠ. ምልክቶችን ፣ የሃገራችንን እና የክልላችንን የባንዲራ ቀለማት የቤተሰቦቻችንን እንዲሁም የጓደኞቻችንን የልብስ ቀለማት መለየት

ቀለም የአንድን ማህበረሰብ አኗኗር ባህል እና እሴት አጉልቶ ለማሳየት ትልቅ ጠቀሜታ አለው። አንድ ማህበረሰብ ደስታውን ሃዘኑን እንዲሁም መንፈሳዊ ህይወቱን በተለያዩ ቀለማቶች ይገልፃል። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ እያንዳንዳችን የምንወደና የማንወደው ቀለም በውስጣችን ሊኖር ይችላል። ለመውደዳችንም ይሁን ለመጥላታችን መንስኤ የሚሆነው የምንኖርበት አካባቢ ፣ ያደግንበት ባህል እንዲሁም ሌሎች ምክንያቶች ሊኖሩን ይችላሉ። ሆኖም ግን የቀለማት ምርጫችን በምንኖርበት ማህበረሰብ ላይ ተመስርቶ እናገኘዋለን። የህፃናት የቀለም ምርጫ ከአዋቂዎች ይለያል። ብዙ ጊዜ የህፃናት የቀለም ምርጫቸው ደማቅ የሆነ ቀለም (ቢጫ ፣ ሰማያዊ ፣ ቀይ) ሲሆን አዋቂዎች ደግሞ ደብዘዝ ያሉ ቀለማትን (ነጭ እና ጥቁርን ጨምሮ) በብዛት ያዘወትራሉ። ህፃናትን አልባሳት ለመግዛት የልብስ መሸጫ ሱቅ/መደብር አስገብተን እንዲመርጡ ብናደርጋቸው መጀመሪያ የሚመርጡት ልብስ የሚወዱት ቀለም ነው ማለት እንችላለን። የቀለም ምርጫችን እንደየ እድሜ ደረጃችንም ጭምር የተለያየ ነው። ነጭ ቀለምን ከሌሎች ቀለማቶች ጋር በማሰባጠር በብዙ የሃገራችን ባህላዊ አልባሳት ላይ ይጠቀሙበታል። የከፋ ፣ ሃድያ ፣ የወላይታ ፣ የጉራጌ ፣ የአሪ ፣ ... ወዘተ የባህል ልብሶች ውስጥ ነጭ ቀለምን ከሌሎች ቀለማቶች ጋር በመቀላቀል ባህላዊ ልብሶችን በመስራት ያስውባሉ።

ስነ-ጥበብን የምንጠቀምበት ስዕል ብቻ ለማስተማር ሳይሆን ተጓዳኝ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በማንሳት ለማስተማርና በቀላሉ መልዕክትን በማስተላለፍ ስዕል እንዳንረሳው ያደርጋል። ለምሳሌ የተያዩ ስዕሎችን በመጠቀም ስለ አካባቢ ንጽህና ፣ ስለ ኮሮና ቫይረስ ፣ ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ እንዲሁም ተያያዥ ወቅታዊ ጉዳዮችን በስዕል ፣ በቅርፃ ቅርፅ እንዲሁም በፖስተር መልክ መልዕክቶችን ማስተላለፍ እንችላለን። የተለያዩ

ስዕላዊ መልዕክቶችን መንገድ ዳር ፣ በእምነት ቦታዎች ፣ በሆስፒታሎች ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ እንዲሁም በልዩ ልዩ ቦታዎች በማስቀመጥ መልእክቶችን በቀላሉ ማስተላለፍ እንችላለን:: ለምሳሌ ከታች በምስሉ ላይ ያለውን ምልክት ልጆች በቤታቸው ውስጥ ፣ በትምህርት ቤታቸው ፣ እንዲሁም በመኖሪያ አካበቢያቸው ስእላዊ መግለጫዎችን በመለጠፍ ማስክ በማድረግ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በቀላሉ መልክቶችን ማስተላለፍ እንችላለን::



ምስል 3.5- ከኮሮና ቫይረስ ራሳችንን እንድንጠብቅ የሚያስጠነቅቅ ምልክት



ምስል 3.6- ራሳችንን ከመኪና አደጋ እንድንጠብቅ የሚያስጠነቅቅ ምልክት

ተማሪዎች ራሳቸውን ከትራፊክ አደጋ እንዲጠብቁ ለማድረግ የተለያዩ ማስጠንቀቂያዎችን ትምህርት ቤት አካባቢ ፣ መኪና መንገድ ዳር እንዲሁም መማሪያ መጽሃፍት ላይ በማስተማር እንዲጠነቀቁ ለማድረግ ምልክቶች ጠቀሜታ አላቸው::

በተጨማሪም ተማሪዎች አርዓያ የሚያደርጓቸውን ሰዎች ፣ ተመራማሪዎች ፣ ታዋቂ ግለሰቦች እንዲሁም ታሪካዊ ቦታዎች በደብተር ላይ እንዲሁም በትምህርት ቤት ግድግዳዎች ላይ ተስለው ስንመለከት ተነሳሽነትን እና

የወደፊት ህልምን እውን ለማድረግ ያግዛል:: ሃይሌ ገብረስላሴን ስንመለከት በሩጫ ስኬታማ ስለመሆን ፣ ጸጋዬ ገበረመድህንን ስንመለከት ደራሲ ስለመሆን ፣ የአፈወርቅ ተክሌን ፎቶ እና ስዕሎች ስንመለከት ደግሞ ስመጥር ሰዓሊ ስለመሆን ፣ የአክሱምን ሃውልት ስንመላከት የቀደምት ስልጣኔዎችን ... ወዘተ ስንመለከት እንደነሱ ለመሆን ጠንክረን መማር እና መስራት እንዳለብን እንረዳለን::

መልመጃ 3.5

- በአካባቢያችሁ በበዓላት ወቅት ሰዎች በብዛት የሚለብሷቸው የቀለም አይነቶችን እና ምክንያታቸውን ዘርዝሩ
- በምትኖሩበት አካባቢ እና በምትማሩበት ትምህርት ቤት አካባቢ የሚገኙ ምልክቶችን በመሳል ለመምህራችሁ አሳዩ
- የተለያዩ መልዕክት ያላቸውን ምልክቶች በመሳል ለመምህራችሁ አሳዩ

## 3.1.2. ሙዚቃ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጠቀሜታ

### መግቢያ

በዚህ ርዕስ ተማሪዎች ሙዚቃ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ይረዳሉ:: ይህም ሙዚቃ የአንድን ማህበረሰብ የኑሮ ሁኔታ ፣ ባህል ፣ እምነት እና የዕለት ከዕለት የኑሮ ሁኔታን አጉልቶ ለማሳየት የሚኖረውን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ::

ሙዚቃ ህብረተሰቡን ስለ አከባቢያቸው ባህል ፣ ወግ እንዲያውቁ በማድረግ ትልቅ ሚናን ይጫወታል:: ሙዚቃ አእምሮን ከማነቃቃት እና ከማዝናናት በተጨማሪ ባህልን ፣ ወግን ፣ እና የኑሮ ሁኔታን በግጥም እና በዜማ መልክ በማዋሃድ ለረጅም ዘመናት እንዲቆይ የማድረግ አቅም አላው:: ሙዚቃ ከኮንሰርት አዳራሽ ባሻገር የማህበረሰቡን የደስታ ፣ የሃዘን ፣ የስራ እንዲሁም የባህል እሴቶችን ለመጠበቅ ጉልህ ድረሻ አለው::

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች ሙዚቃ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይረዳሉ

- ለሰላም ፣ ለሃዘን ፣ ለደስታ እንዲሁም ለሀገር የተዘመሩ መዝሙሮችን ያውቃሉ
- አካባቢያዊ እውቀቶችን በመጠቀም መዝሙሮችን ይዘምራሉ
- የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊ ዘፈኖች እና ውዝዋዜዎችን ይረዳሉ

## የማነቃቂያ ጥያቄ

- ስለ ሃገር ከተዘመሩ መዝሙሮች ውስጥ የምታውቁትን በማስታወስ ዘምሩ

ሙዚቃን ከዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቻችን ጋር አብሮ በማጣመር የኑሯችን አንዱ መገለጫ ማድረግ እንችላለን:: ሙዚቃ በእለት ከእለት የኑሮ እንቅስቃስያችን የደከመን አእምሯችንን ለማሳረፍ ፣ ስነ-ቃሎችን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲሁም የሃገር ፍቅርን ለመግለጽ ያግዛል::

## መልመጃ 3.6

- ተማሪዎች ማህበረሰቡ ለተለያዩ ኩነቶች የሚጠቀሟቸውን መዝሙሮች በመዘመር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ

## ሀ. አካባቢያዊ ጥበቦችን በመጠቀም መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን መከወን

አከባቢያዊ ጥበቦች በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የተሰሩ እና የተለመዱ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሚሰሩ ዜማዎችን ለማወቅ ያግዘናል:: ለምሳሌ ክራር ፣ መሰንቆ ፣ ዲታ ፣ ከበሮ ፣ ዲንክያ (ድንካ) ፣ ባህላዊ የውዝዋዜ አልባሳት እና የተለያዩ ለባህላዊ ክንውኖች በመጠቀም የሚደረግ ሙዚቃዊ ተግባር ነው:: ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በምንጫወትበት ጊዜ ትክክለኛውን የባህል አልባሳት በመልበስ ውዝዋዜዎች በግልም ሆነ በቡድን በማድረግ ደማቅ ትርኢት ለማሳየት ይጠቅማል::

በሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ ባህላዊ ዘዴዎችን በመጠቀም አከባቢያዊ ሙዚቃዎችንና ውዝዋዜዎችን የሚከውኑ ማህበረሰቦች ይገኛሉ::ለምሳሌ በሃላባ አካባቢ ጣርቤተ (ከረቡታ) የሚባለውን የሙዚቃ መሳሪያ በተለያየ ባህላዊ ከንዋኔዎች በሚያደረጉበት ወቅት ሰዎች በቡድን ሆነው ለተለያዩ ዝማሬዎች ማድመቂያ ይጠቀሙበታል:: ይህ የሙዚቃ መሳሪያ ልክ እንደ እንስራ በሸክላ

የሚሰራ ሲሆን አፉን በጨርቅ፣ በቆዳ ወይን በፕላስቲክ በመሸፈን ልክ እንደ ከበሮ ይጠቀሙበታል።



ምስል 3.7- የሃላባ ባህላዎ ሙዚቃ መሳሪያ ሲጫወት የሚያሳይ ምስል



ምስል 3.8- የሃላባ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ከረቡታ በጋራ ሲጫወቱ

## መልመጃ 3.7

◆ በሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢያዊ ሙዚቃዎችን እናገኛለን። ከዚህ በመነሳት ተማሪዎች በአከባቢያችሁ የሚገኙ ባህላዊ መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን በመስራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## ለ. የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊ ዘፈኖችን እና ውዝዋዜዎችን መከወን

### የማነቃቂያ ጥያቄ

♣ በአካባቢያችሁ የሚታወቁ ባህላዊ ዘፈኖችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ

በሃገራችን ኢትዮጵያ ሃገረሰባዊ ዘፈኖች እና ውዝዋዜዎች በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በተለያየ ወቅት የሚከወኑ ዜማዎች ናቸው:: እነዚህም ዜማዎች በስራ ጊዜ ፣ በሰርግ ፣ በለቅሶ እንዲሁም በበዓላት ጊዜ የሚዘፈኑ ሊሆኑ ይችላሉ:: የዘፈኖቹ ሁኔታ በእንደየ ማህበረሰቡ የኑሮ እና የባህል ልዩነት በተለያየ መንገድ ይከናወናሉ:: በአብዛኛው የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊ (ባህላዊ ዘፈኖች) የሚባሉት በቤተሰብ ፣ በጎሳ ፣ በማህበረሰብ ወይም በሌላ ቅርብ በሆነ ቡድን አውድ ውስጥ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ማለትም ስራ በሚሰራበት ወቅት ፣ እርሻ በሚታረስበት ወቅት እና በደቦ ለስራ በሚሰባሰቡበት ጊዜ የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊ መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን ያካትታል::

ከእነዚህም መካከል በአብዛኛው የኢትዮጲያ ክፍል በተለያዩ የስራ ወቅት ለምሳሌ በእርሻ ወቅት የአካባቢው ማህበረሰብ ለእርሻ ሲወጡ በመሰባሰብ የእርሻ መሳሪያዎችን በመያዝ በጋራ የስራ ሙዚቃዎችን እያዜሙ በተጨማሪም በስራ ላይ ያሉትን ሰዎች ለማበረታታት በመወዛወዝ ስራዎቻቸውን ይከውናሉ::

ከሚከወኑ የስራ ዘፈኖች በጥቂቱ እንመለከታለን

### በሬ እና ገበሬው

በሬው እሸሩሩ በሬው እሸሩሩ
እንግዲ በርታልን ደረሰ መኸሩ
አቻምና እና አምና እንዲሁም ዘንድሮ
ምርቱንም ከማሳ ጎመኑን ከጓሮ
በአንተ ድካም በላን እኛም እንደድሮ
ገበሬውም ስማኝ እርሻህንም እረስ
ዘርህንም ዘርተህ በሚገባ አድርስ
የድካምህ ፍሬ ለህገሬው እንዲደርስ
አዝመራህን ሰብስብ ምርትህንም እፈስ



ምስል 3.9- እርሻ በማረስ ላይ ያለ ገበሬ

መልመጃ 3.8

- ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ማህበረሰቡ በስራ እና በተለያዩ ክንውኖች የሚጠቀማቸውን የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜዎችንና ዘፈኖችን በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ::

## 3.1.3.የትወና ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው ጠቀሜታ

በዚህ ርዕስ ተማሪዎች የእይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታዎች እንመለከታለን:: የእይታ ጥበብ ድራማን ፣ ትያትርን እንዲሁም ግጥማዊ መነባንቦችን በመጠቀም ልዩ ልዩ ሃሳቦችን ማስተላልፍ እንችላለን:: ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚመለከቷቸውን ባህላዊ ክንዋኔዎች ፣ ማህበራዊ ችግሮችን እንዲሁም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን በድራማ ፣ በትያትር እንዲሁም በመነባነብ ማሳየት ይችላሉ:: የትውን ጥበባት ከንግግር እና ከጽሁፍ ባለፈ ሰዎችን እየተዝናኑ ቁምነገር እንዲጨብጡ ለማድረግ አይነተኛ መንገድ ነው:: ስለሆነም ተማሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ ፣ በትምህርት ቤታቸው አካባቢ እንዲሁም በእምነት ተቋማት አካባቢ የተመለከቷቸውን ሁኔታዎች እንደ መነሻ ሃሳብ በመውሰድ ተውኔቶችን ማቅረብ ይችላሉ::

መልመጃ 3.9

- ተማሪዎች በምትኖሩበት አካባቢ በባህላዊ መንገድ የተጣሉ ሰዎችን ሽማግሌዎች እንዴት እንደሚያስታርቁ አጭር ድራማ በመስራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ

## ማጠቃለያ

በምዕራፍ ሶስት የትውን እና ዕይታ ጥበባት ለማበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ተመልክተናል:: ሙዚቃ ፣ ስዕል ፣ ትያትር ፣ ድራማ እና ፎቶግራፍ የአንድን ማህበረሰብ የታሪክ ፣ የባህል ፣ እንዲሁም የአስተሳሰብ ደረጃን ለማሳየት ትልቅ ሚና አላቸው:: ይህም ማለት ባህልን ለመጠበቅ እንዲሁም ለማስተዋወቅ ፣ ታሪክን ለመመዝገብ እና ለማጥናት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው:: ስለዚህ የትውን እና ዕይታ ጥበባትን ከማህበረሰቡ የእለት ተእለት ኑሮ ነጥለን ማየት አንችልም::

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. ተማሪዎች የተለያዩ አካባቢዎችን ባህላዊ ውዝዋዜዎች ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩዋቸው
2. በአከባቢያችሁ የሚገኝ አከባቢያችሁን የሚገልፅ የትንፋሽ ፣ የስልተ-ምት ፣ የክር የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጫወት ዘርዝሩ
3. የእይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጥቅም ዘርዝሩ
4. የትውን ጥበባት ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

# ምዕራፍ አራት

# አድናቂነት

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የትውን እና የእይታ ጥበባትን ማድነቅን ፣ መለማመድን እና መገምገምን በስፋት እናያለን:: ሀገር በቀል እውቀቶችን በማድነቅ በተለያዩ የእይታና የትውን ጥበባት ውስጥ መለማመድ እና ማሳደግ አስፈላጊ ነው:: ተማሪዎች ስዕልን ፣ ሙዚቃን ፣ ትያትርን እና ውዝዋዜን ደጋግመው ሲለማመዱ የሚያገኙትን ጥቅም እንዳስሳለን:: ስልጣኔ ማለት የነበረውን ሃገረሰባዊ እውቀት በሌላ ሃገር ባህል መተካት ሳይሆን በእውቀት ደግፎና ተንከባክቦ ማሳደግ ስለሆነ በአካባቢያችን የሚገኙ ሃገረሰባዊ እውቀቶችን ለማሳደግ ከማድነቅ እንጀምራለን::

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ

- ሃገር በቀል እውቀቶችን ያደንቃሉ
- መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን ይለማመዳሉ
- ፎቶ ማንሳት ይለማመዳሉ

- ግለ-ተውኔት/መነባንብ ያቀርባሉ/ይጽፋሉ
- ሃገረሰባዊ የቤት አሰራር አይነቶችን ያውቃሉ

## 4.1. የትውን እና የእይታ ጥበባት በአፈፃፀምና በምስል ጥበባት ውስጥ ደጋግሞ የመለማመድ ውጤት

### መግቢያ

በዚህ ርዕስ ስር የተለያዩ ድራማዎችን ፣ መነባንቦችን እንዲሁም ግጥሞችን ደጋግመን በመለማመድ እንዴት መድረክ ላይ ማቅረብ እንደምንችል እንማራለን:: ደጋግሞ መለማመድ ወደ እንከን የለሽ ብቃት ስለሚያሳድግ ተማሪዎች ይህንን ተረድተው እንዴት መለማመድ እንዳለባቸው እንመለከታለን:: ስለሆነም በዚህ ርዕስ ስር የተለያዩ ተውኔቶችን እና ደጋግመን በመለማመድ እንዴት መድረክ ላይ በጥሩ ሁኔታ እንደምናቀርብ እንማራለን::

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች


- ተማሪዎች የትውን እና የዕይታ ጥበባትን ደጋግመው ይለማመዳሉ
- ስዕልን ፣ ሙዚቃንና ተውኔትን ደጋግመው በመለማመድ የሚያገኙትን ጥቅም ይረዳሉ
- የእይታ ጥበባትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያውቃሉ
- ደጋግመው በመለማመድ ችሎታቸውን ያሳድጋሉ
- ችግር ፈቺ ጥናቶችን እና ምርምሮችን እንደ አቅማቸው መስራትን ይለማመዳሉ
- ደጋግመው በመስራት በራስ መተማመናቸውን ያዳብራሉ
- ተማሪዎች ድራማን እና ትያትርን ደጋግሞ በመለማመድ ችሎታቸውን ያዳብራሉ
- በራስ መተማመናቸውን ያዳብራሉ
- ተማሪዎች መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን ይለማመዳሉ
- መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን በተደጋጋሚ በመለማመድ ችሎታቸውን ያዳብራሉ

## የማነቃቂያ ጥያቄ

- ብዙ ጊዜ ደጋግማችሁ የምትሰሩትን ስዕል ለመምህራችሁ ተናገሩ ወይም ስላችሁ አሳዩ

ደጋግሞ መስራት ፍጹም ያደርጋል እንደሚባለው ሁሉ አንድን ኪነ-ጥበባዊ ክንዋኔ በተደጋጋሚ በተለማመድን ቁጥር የማድነቅ አቅማችንን በዚያው ልክ እናሳድጋለን:: የነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ እንደሚባለው አባባል በደንብ ያልተለማመድነውን ድራማ ወይም ሙዚቃ መድረክ ላይ ብናቀርብ ሊበላሽብን ወይም ልናፍርበት እንችላለን ማለት ነው:: ከዚህ ቀጥሎ ስዕልን ሙዚቃን እና ድራማን ደጋግሞ መለማመድ የሚሰጠውን ጥቅም ሰፋ አድርገን እንመለከታለን:: ስዕልን በተደጋጋሚ ለረጅም ጊዜ ለመስራት ከፈለግን ሁልጊዜ ከቀላል ወደ ከባድ መሄድ አስፈላጊ ነው:: በመጀመሪያ ቀላል መስመሮችን በማስመር ወደ ንድፍ ስዕል እናሳድገዋለን:: አንድን ነገር አይተን የመሳል/የመንደፍ ችሎታችንን ካዳበርን በኋላ ቀላል ቀለማቶችን እንዴት መቀባት እንድምንችል እናያለን:: በመቀጠል ደግሞ የቀለማቶቹን ባህሪያት ለመረዳት ቀለም እንዴት እንደሚቀላቀል እና እንደሚቀባ በሂደት እንገነዛባለን:: እንዲህ እንዲህ እያልን መስራት የምንፈልገውን የስዕል አይነት እስከምንሰራ ደረጃ በደረጃ የስነ-ጥበብ አይነቶችን እንማራለን ማለት ነው:: ሙዚቃም ሆነ ድራማ ከላይ እንደጠቀስነው ደረጃ በደረጃ በተደጋጋሚ በመለማመድ የምንፈልገውን ችሎታ የምናዳብርበት ሂደት ነው::

ምሳሌ:- ከታች ያለውን ምስል ደጋግማችሁ በመሳል ያገኛችሁትን ጥቅም ዘርዝሩ



ምስል 4. 1- የዝሆኖች ምስል

መልመጃ 4.1

- የትውን እና ዕይታ ጥበባትን ደጋግሞ መለማመድ የሚያስገናቸውን ጥቅሞች ዘርዝሩ

## 4.1.1.የእይታ ጥበባትን ደጋግሞ መለማመድ

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች የመረጣችሁትን የስዕል አይነት አምስት ጊዜ ደጋግማችሁ ሳሉት፡፡ አምስቱን ስዕሎች በማወዳደር የተሻለውን ምረጡ፡፡

ሥዕል መስራት የሚጀመረው ከመሞነጫጨር ሲሆን ወደ ትላልቅ የሸራ ላይ ስዕል እና ቅርፃ ቅርፅ ያድጋል፡፡ ስዕል መሳል በአንድ ቀን ወይም በአንድ ወር የሚለመድ ሳይሆን በሂደት ለወራት አለዚያም ለአመታት ተለማምደን የምናገኘው ችሎታ ነው፡፡ ሥዕልን ደጋግሞ በመለማመድ የሚከተሉትን ጥቅሞች እናገኛለን፡፡

### ሀ. ችሎታን ለማሳደግ

የሥዕል ችሎታ ሁልጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚቀጥል ሳይሆን ደጋግመን ከሰራን ችሎታችን በሚገርም ሁኔታ እንዲጨምር ሲያድርግ በተቃራኒው ካልሰራን ደግሞ ችሎታችን ቀስ በቀስ እየጠፋ ይሄዳል ማለት ነው፡፡ ስዕልን ደጋግሞ መስራት ከችሎታ በተጨማሪ የማሰብ ፣ የማሰላሰል እና የመፍጠር ችሎታችንን ለማሳደግ ያግዘናል፡፡

### ለ. ችግር ፈቺ ፈጠራዎችን ለመስራት

ብዙ መመራመር አዳዲስ ፈጠራዎችን እና ያልተሞከሩ ግኝቶችን ለመስራት ያግዛል፡፡ ተደጋጋሚ ሙከራ ለአንድ ችግር ካንድ በላይ አካባቢያዊ መፍትሄዎችን ለመፍጠር ያስችላል፡፡

### ሐ. ለመዝናናት

ሥዕል ለማህበረሰቡ ችግር ፈቺ ፈጠራዎችን ከመስራት በተጨማሪ ለመዝናኛነት ያገለግላል፡፡ ስዕል ሙዚቃ ወይም ድራማ ትልቁ ጥቅማቸው ሰዎች እየተዝናኑ እንዲማሩ ማድረግ ነው፡፡ በአካባቢያችን ያሉትን ነገሮች ወይም በጭንቅላታችን የምናስበውን ነገር ወደ ስዕል ብንቀይረው ትልቅ የአዕምሮ ረፍት/ደስታን

እናገኛለን። ስዕል መሳል ለሰአሊዎች ብቻ ሳይሆን ሁሉም ሰው እንደ እድሜ ደረጃው እና ችሎታው ራሱን ለማስደሰት ቢሰራ ከፍተኛ እርካታን ያስገኝለታል ማለት ነው።

### መ. በራስ መተማመንን ለማዳበር

ኪነ ጥበብ በባህሪው ሰዎች በሚሰበሰቡበት መድረክ ላይ የሚቀርብ በመሆኑ ተማሪዎች የመናገር ፣ የማድመጥ እና የመከወን ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ትልቅ እድል ይከፍታል። በሀገራችን ኢትዮጵያ ስመጥር የሆኑ ሙዚቀኞች ፣ ደራሲዎች ፣ ሰዓሊዎች እንዲሁም ተዋናዮች መነሻቸው የትምህርት ቤት መድረኮች እንደሆኑ ይናገራሉ። በዚህ የ4ኛ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች የጻፉትን ግጥም ለክፍል ጓደኞቻቸው በማቅረብ ፣ የሳሉትን ስዕል ግድግዳው ላይ በመለጠፍ ሌሎች ተማሪዎች እንዲያዩት በማድረግ ፣ ቀልድ በማቅረብ ፣ ባንዲራ ሲሰቀልና ሲወርድ መዝሙር በመዘመር ቢለማመዱ ወደፊት ትልቅ ቦታ ይደርሳሉ። ስለዚህ የትምህርት ቤት ሚኒሚድያዎች ላይ የተለያዩ ዝግጅቶችን በማቅረብ በራስ መተማመናችሁን ማሳደግ ከእናንተ ይጠበቃል።

#### መልመጃ 4.2

- ተማሪዎች አንድን የድመት ስዕል አምስት ጊዜ ደጋግማችሁ በመሳል ለመምህራችሁ አሳዩ

## 4.1.2.የትውን ጥበባትን ደጋግሞ መለማመድ

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት ድራማ ሰርታችሁ ታውቃላችሁ? ሰርታችሁ ከሆነ ከማቅረባችሁ በፊት ስንት ጊዜ ተለማመዳችሁት? ለጓደኞቻችሁ አስረዱ

በዚህ ምዕራፍ የትውን ጥበባትን ደጋግሞ መለማመድ በተማሪዎች ችሎታ ላይ የሚኖረውም ሚና እንመለከታለን። የትውን ጥበባት ከሚባሉት ውስጥ ሙዚቃ እና ትያትር (ድራማ) ዋነኞቹ ናቸው። አንድን ሙዚቃ ወይም ድራማ መድረክ ላይ ከማቅረባችን በፊት ለብዙ ጊዜ ደጋግመን እንለማመደዋለን። ድራማ ለመስራት የተለያዩ አልባሳትን ከማሰባሰብ ጀምሮ የድራማውን ዋና

ዋና ሃሳቦች በቃላችን (ያለምንም ወረቀት) መሸምደድ መቻልን ያጠቃልላል:: ተማሪዎች የሸመደዱትን ነገር ደግሞ እንዳይጠፋባቸው እና ለተመልካቾች በምን አይነት ተውኔት ማሳየት እንዳለባቸው ደጋግመው ማሰብና መለማመድ ይጠይቃል:: ሌላው ደጋግሞ የመለማመድ ጥቅም መድረክ ለማቅረብ ፍርሃት ካለባቸው እንዲያስወግዱ ያግዛቸዋል:: አንድ ጀማሪ ሰው ለመጀምሪያ ጊዜ ብዙ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ ድራማ ሲያቀርብ ፍርሃት ሊታይበት ይችላል:: ስለዚህ በራስ መተማመንን ለማዳበር ደጋግሞ መለማመድ ትልቁ መፍትሄ ነው:: ድራማን ደጋግሞ መለማመድ የሚከተሉትን ጥቅሞች ያስገኛል::

## ሀ. ጊዜን ለመቆጠብ

ለብዙ ጊዜ የተለማመድነውን ድራማ በሰዎች ፊት ለማቅረብ ብዙ ጊዜ እንዳይወስድብን ያግዛል:: አንድ ድራማ ወይም ተውኔት በአጭር ጊዜ ማቅረብ ተመልካቾች እንዳይሰለቹ በማድረግ በቀላሉ የምንፈልገውን መልዕክት ማስተላለፍ እንችላለን::

## ለ. ወጪን ለመቀነስ

አንድ ድራማ በረዘመ ቁጥር የጊዜ እና የገንዘብ ብክነትን ስለሚያስከትል በአጭሩ ማቅረብ ሁልጊዜ የሚመከር ተግባር ነው:: በተለይ ተማሪዎች ለክፍል ጓደኞቻቸውም ሆነ ለትምህርት ቤታቸው ማህበረሰብ ድራማ ማቅረብ ሲፈልጉ አጭር እና ግልፅ በሆነ መገድ ቢያቀርቡ ይመከራል::

## ሐ. የድራማውን ጭብጥ በደንብ ለመገንዘብ

በተደጋጋሚ መለማመድ የተውኔቱን ዋና ሃሳብ ጎልቶ እንዲወጣ ለማድረግ በተለያዩ የሰውነት እንቅስቃሴዎቻችን እንድናሳይ እድል ይሰጠናል::

### መልመጃ 4.3

- አንድን ድራማ በትክክል ሳንለማመድ መድረክ ላይ በማቅረብ ብንሞክር ምን አይነት ጉዳት እንዳለው ተወያይታችሁ አቅርቡ
- በደንብ ሳይለማመዱ ድራማ ሲያቀርቡ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ

## 4.1.3.መዝሙርንና ውዝዋዜን ደጋግሞ የመለማመድ ውጤት

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ለወላጆች በዓል ግጥም እና ውዝዋዜ አቅርባችሁ ከሆነ እንዴት እንደተለማመዳችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ

በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች መዝሙርን እና ውዝዋዜን ደጋግመን በመለማመዳችን የምናገኛቸውን ጥቅሞች እንማራለን:: መዝሙር እና ውዝዋዜ በባህሪው ብዙ ልምምድ የሚጠይቅ በመሆኑ ችሎታችንን ለማሳደግ ደጋግመን ብንለማመድ የምናገኘውን ጥቅም እንረዳለን:: በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች መዝሙርን እና ውዝዋዜን ደጋግመን በመለማመዳችን የምናገኛቸውን ጥቅሞች እንማራለን:: መዝሙርን የሚለማመዱት ከህፃንነታቸው ጀምሮ ነው:: ይህ ማለት መዝሙርን መለማመድ የሚጀምሩት ከመስማት ሲሆን በአካባቢያቸው የሚታወቁ እና የተለመዱ መዝሙሮችን በመዘመር ይለማመዳሉ:: ልጆች መዝሙርን መስማት የሚጀምሩት እናታቸው ወይም አባታቸው እንዲተኙላቸው ፣ ምግብ እንዲበሉላቸው ፣ እንዳያለቅሱባቸውና እንዲጫወቱላቸው ለማድረግ በሚሞክሩበት ሂደት ውስጥ ነው:: መዝሙሮች በህፃናት አዕምሮ ውስጥ መቀረፅ የሚጀምሩት ገና በለጋነታቸው ነው:: ድምጽ እና መዝሙር ቀስ በቀስ ወደ ውስጣቸው በማስገባት በመዘመር ይለማመዳሉ:: ከመዝሙር በተጨማሪ ውዝዋዜዎችንም በአካባቢያቸው ከሚገኙ የሰዎች ፣ የእስሳት እንዲሁም የዕፅዋት እንቅስቃሴ በመነሳት ማስመሰል እና መለማመድ ይጀምራሉ:: ሰዎች በእነዚህ የመለማመድ ሂደት ውስጥ ታዋቂ ሙዚቀኛ ወይም ታዋቂ ተወዛዋዥ የመሆን እድላቸው ሰፊ ይሆናል:: የሰው ልጆች መዝሙርን በሚዘምሩበት ጊዜና ውዝዋዜን በሚወዛወዙበት ጊዜ ከተለያዩ ሃሳቦችና ጭንቀቶች እራሳቸውን ነፃ ከማድረግም ባለፈ ከጭንቀት ከሚመጡ በሽታዎች እራሳቸውን ይጠብቃሉ::

### መልመጃ 4.4

- ተማሪዎች የተለያዩ መዝሙሮችን በቡድንና በግል በመሆን ውዝዋዜዎችንም ተለማምዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ

## 4.2. ሃገር በቀል የቤት አሰራርን እና ማስጌጥን፤ የሙዚቃ ጨዋታዎችንና ውዝዋዜዎችን እንዲሁም ድራማዊ እንቅስቃሴዎችን እውቅናና አድናቆት መስጠት

### መግቢያ

የቤት አሰራር አይነቶች የአንድን ማህበረሰብ ባህል እና የኑሮ ሁኔታ በከፊል ያሳያሉ፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ እጅግ ብዙ አይነት የቤት አሰራር አይነቶች እና ስም አላቸው፡፡ ስለሆነም የቤት አሰራር አይነቶች እንደየ ባህሉ ወይም እንደ ማህበረሰቡ ፍላጎት የሚወሰን ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የቤት አሰራሮችን ምሳሌ በማንሳት እንማራለን፡፡ ሀገረሰባዊ የሙዚቃ ጨዋታዎችን እውቅናና አድናቆት መስጠት ባህላችንን ለማወቅ እና በባህላችን እንድንኮራ ስለሚያደርገን በሚገባ ልናውቅ ያስፈልጋል፡፡

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ

- በአካባቢያቸው እና በሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ የቤት አሰራር አይነቶችን ይረዳሉ
- ሀገር በቀል እውቀቶችን ያደንቃሉ
- ተማሪዎች ፎቶ ማንሳት ይለማመዳሉ
- የተለያዩ ስዕሎችን በመሳል ይለማመዳሉ
- በመዝሙር እና ውዝዋዜ ስለ ሀገራቸው ባህልና ወግ በሚገባ ይረዳሉ
- ሀገር በቀል የሙዚቃ ጨዋታዎችን ያውቃሉ ፣ ይዘምራሉ

### 4.2.1. ሀገረሰባዊ የቤት አሰራር አይነቶች

#### የማነቃቂያ ጥያቄ

♣ የጎጆ ቤት እና የቆርቆሮ ቤት ልዩነት ምንድን ነው? አብራሩ

የቤት አሰራር አይነቶች የአንድን ማህበረሰብ ባህል እና የኑሮ ሁኔታ በከፊል ያሳያሉ፡፡ በሃገራችን ኢትዮጵያ እጅግ ብዙ አይነት የቤት አሰራር አይነቶች እና

ስሞች አሉ። ስለሆነም የቤት አሰራር አይነቶች እንደየ ባህሉ ወይም ፍላጎት የሚወሰን ነው። ከዚህ ቀጥሎ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የቤት አሰራሮችን ምሳሌ በማንሳት እንማራለን።

ሀገረሰባዊ የቤት አሰራር አይነቶች እንደየ ባህላችን ፣ የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም የአየር ፀባይ አይነት  የተለያየ ነው። ደጋማ (ቀዝቃዛ) በሆኑ አካባቢዎች የሚሰሩት የቤት አይነቶች ቅዝቃዜን ለመቋቋም (ሙቀትን እንዲፈጥር) ተደርጎ ሲሰራ ፣ ቆላማ (ሞቃታማ) በሆኑ አካባቢዎች ደግሞ በቂ ነፋስ እንዲገባ ታሳቢ በማድረግ ብዙ መስኮቶች እና ቀዳዳዎች እንዲኖሩት ተደርጎ ይሰራል። አብዛኛው የደቡብ ኦሞ አካባቢዎች በጣም ሞቃታማ በመሆናቸው የቤት አሰራር አይነቶች በቀላሉ የሚሰሩ ጎጆዎች ሲሆኑ ነፋስ ወደ ውስጥ እንዲገባ በማሰብ ግድግዳዎቹ ክፍት ይሆናሉ ማለት ነው። በተቃራኒው ደጋማ በሆኑ የሃድያ እና የወላይታ አካባቢዎች ደግሞ ሙቀት ከቤት ውስጥ እንዳይወጣ አፍኖ ለማስቀረት ሲባል ትንሽ የሆኑ በርና መስኮቶች ያላቸው ሲሆን በአብዛኛው ደግሞ ዙሪያቸውን በጭቃ የተመረጉ ወይም በሲሚንቶ የተገነቡ ይሆናሉ ማለት ነው።



ምስል 4.2- የጉራጌ ባህላዊ የቤት አሰራር

ቤቶቹ ከተሰሩ በኋላ የበለጠ ምቹ እና ማራኪ ለማድረግ የተለያዩ ባህላዊ የቤት ማስዋቢያዎችን ይጠቀማሉ። ከነዚህ ማስዋቢያዎች መካከል በእበት እና በአመድ መለቅለቅ ፣ ቀለም መቀባት እንዲሁም ቤጣጌጦችን መስቀል ነው። ባህላዊ የቤት አሰራሮች ከውበታቸው በተጨማሪ ለረጅም አመታት እንዲያገለግሉ ታሳቢ ተደርገው ይሰራሉ። ለምሳሌ በስልጤ ፣ በጉራጌ ፣ በኮንሶ ፣ በከፋ እና በሌሎች አካባቢዎች የሚሰሩ ጎጆ ቤቶች እና የቆርቆሮ (የጭቃ) ቤቶች ለረጅም ጊዜ ሊያገለግሉ ይችላሉ። በተቃራኒው አርብቶ አደር በሆኑ የደቡብ ኦሞ አካባቢዎች ደግሞ ሰዎች በቋሚነት አንድ ቦታ ስለማይኖሩ የሚሰሩት ቤቶች ለአጭር ጊዜ ብቻ እንደሚቆዩ ታሳቢ ያደረጉ ናቸው ማለት ነው።



ምስል 4.3 ደቡብ ኦሞ አካባቢ የሚዘወተር የጎጆ አሰራር

አንድ የኮንሶ ባህላዊ ጎጆ (ሞራ) እንደ መሰብሰቢያ አዳራሽ የሚያገለግል ሆኖ በመንደሮች መካከለኛ ስፍራ ላይ ይሰራል። ሞራ ጎጆ ረጅም አመታትን እንዲያገለግል ታሳቢ ተደርጎ ስለሚሰራ በአማካኝ ከ30-40 አመታት ሊቆይ ይችላል። ይህ ጎጆ የተጣሉ ሰዎችን ለማስታረቅ ፣ ባህላዊ የንግስና ስርዓቶችን ለመፈጸም እንዲሁም በዓላትን ለማክበር ለሰዎች በጋራ የመሰባበቢያ ቦታ ተደርጎ ይቆጠራል።



ምስል 4.4 የኮንሶ ባህላዊ ጎጆ (ሞራ)



ምስል 4.5- የጋሞ ጎጆ

## መልመጃ 4.5

- ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የሚገኙ የቤት አሰራር አይነቶችን ስላችሁ አሳዩ

## ሀ. ስዕል መሳል እና ፎቶ ማንሳትን መለማመድ

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- የፎቶ ማንሻ ካሜራ በእጃችሁ ይዛችሁ ወይም ፎቶ አንስታችሁ ታውቃላችሁ? ልምዳችሁን ለሌሎች ተማሪዎች አካፍሉ

ስለ ፎቶግራፍ መሰረታዊ ነገሮች በምዕራፍ አንድ በስፋት ስለተመለከትን በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ፎቶ ማንሳት እንዴት እንደምንለማመድ እንማራለን:: ፎቶ ለማንሳት መሰረታዊ የፎቶግራፍ አላባውያንን ማለትም ብርሃን ፣ ቀለም ፣ አወቃቀር እና እንቅስቃሴን በሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ፎቶ ለማንሳት የፎቶ ካሜራ ወይም ተንቀሳቃሽ ስልኮችን ልንጠቀም እንችላለን:: ፎቶ ማንሳት ከመጀመራችን በፊት የምንጠቀምበትን የፎቶ ማንሻ መሳሪያ በደንብ ማወቅ ያስፈልጋል:: መሰረታዊ ከምንላቸው ውስጥ ካሜራ (የስልክ ፎቶ ማንሻ) እንዴት ማብራት እና ማጥፋት እንዳለብ ፣ የካሜራውን ብርሃን እንዴት ማብራትና ማጥፋት እንዳለብን ፣ እንዴት ማቅረብና ማራቅ እንዳለብን እና እንዴት ማንሳት እንደምንችል ዋና ዋናዎቹ ተግባራት ናቸው::

### መልመጃ 4.6


- ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ወይም በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ያሉ ነገሮችን ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ፎቶ በማሳት ወይም በትምህርት ቤት በግቢ ውስጥ የሚገኙ ፎቶዎችን በመመልከት ተወያዩ ተለማመዱ


## ለ. ሥዕል አስመስሎ መስራት መለማመድ

ይሄ ርዕስ ተማሪዎች ፎቶዎችን በመሳል መለማመድ እንዲችሉ ማድረግ ነው:: በመጀመሪያ የስዕል ችሎታን ለማዳበር ፎቶዎችን እያዩ ደግሞ በመስራት ወይም የታዋቂ ሰዓልያንን ስዕል ደግሞ በመስራት መለማመድ ይቻላል:: ቀስ በቀስ ግን የራስን የፈጠራ ስዕል በመስራት ችሎታችንን ማዳበር እንችላለን:: ከዚህ በመቀጠል ሌላ ሰው የሰራውን ስዕል ደግመን በመሳል የማስመሰል ችሎታችንን እናዳብራለን::

### መልመጃ 4.7

- ከታች በምስሉ ላይ ሚታዩትን ስዕሎች አስመስላችሁ ሳሉ





ምስል4.6. ስዕልን ከፎት ላይ መስራት

ምስል 4.7 የተለያዩ አይነት ንድፎች


## ሐ. የተዘጋጀ ህትመት

### ወረቀት ላይ ቆርጦ በማውጣት ማተም

ይህ የህትመት አይነት የተዘፋጀው ወረቀት ላይ በመንደፍ ቀለም እንዲነካ የሚፈለገውን የወረቀት ክፍል ቆርጦ በማውጣት ቀሪውን የወረቀት ክፍል ደግሞ በመተው የሚሰራ ነው:: በመቀጠል ደግሞ የተቆረጠው ወረቀት ስር ሌላ ወረቀት በመደረብ ቀለም በነካ ስፖንጅ ወይም ጨርቅ ባዶ ቦታው ላይ ቀስ በሎ ወለም በመቀባት እስኪደርቅ ጠብቆ በማንሳት ህትመቱን በአዲስ ወረቀት ላይ ማሳየት እንችላለን::



ምስል 4.8- የተዘጋጀ የወረቀት ላይ ህትመት



ምስል 4.9- የተዘጋጀ የወረቀት ላይ ህትመት



ምስል 4.10- የተዘጋጀ የወረቀት ላይ ህትመት

## የድንች ህትመት

የድንች ህትመት የሚባለው ድንችን ሁለት ቦታ ላይ በመሰንጠቅ የምንፈልገን ንድፍ እላዩ ላይ መሳል:: በመቀጠል አላስፈላጊ የሆነውን የድንች ክፍል በምላጭ ቆርጦ በማውጣት ቀለም በመቀባት በጥንቃቄ የተዘጋጀው ወረቀት ላይ ማተም ነው::



ምስል 4.11- የድንች ህትመት




ምስል 4.12- የድንች ህትመት



ምስል 4.13- የድንች ህትመት



ምስል 4.14- የድንች ህትመት



ምስል 4.15- የድንች ህትመት

መልመጃ 4.8

◆ ተማሪዎች ትላልቅ ድንች ይዛችሁ በመምጣት የምትፈልጉትን ንድፍ ሰርታችሁ ወረቀት ላይ ማተም ተለማመዱ

## 4.2.2.ሀገር በቀል የሙዚቃ ማጫወቻዎችን እውቅናና አድናቆት መስጠት

የማነቃቂያ ጥያቄ

◆ ተማሪዎች የምትወዱት የሃገራችን ሙዚቃ/መዝሙር የቱ ነው? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ

ሀገር በቀል የሙዚቃ ጫወታዎችን እውቅናና አድናቆት መስጠት ልጆች የራሳቸውን (የአካባቢያቸውን) ባህልና ወግ በማወቅ የሙዚቃ ጨዋታዎችን በመጫወት ለማያውቁት በማሳወቅ የሀገራቸውን የሙዚቃ ጨዋታዎች እውቅናን እና አድናቆትን እንዲያገኙ ማድረግ ማለት ነው፡፡

በተለያዩ የሃገራችን ክፍሎች ብዙ አይነት ሀገር በቀል የሙዚቃ ጨዋታዎች ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ያህል አዲስ አመትን መሰረት በማድረግ በተደጋጋሚ ከሚዘመሩ መዝሙሮች መካከል አበባ አየሽ ወይ የሚለው ዜማ በህፃናት ዘንድ ተወዳጅ ዜማ ነው፡፡ በአንድ አካባቢ የተለመዱ አካባቢያዊ (ሀገር በቀል) መዚቃዊ ጨዋታዎችን ከትውልድ ትውልድ ከማሸጋገር ባለፈ ለሌላው አካባቢ ለማሳወቅ እና አድናቆት ለመስጠት ነው፡፡

ምሳሌ4.1

አበባ አየሽ ሆይ በብዙ የሃገራችን አካባቢዎች በአዲስ አመት ወቅት በሴት ልጆች የሚዘመር መዝሙር ሲሆን ሙሉ ግጥሙ እንደሚከተለው ተጽፏል፡፡

አበባ አየሽ ወይ

ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን
ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን
እማማ አሉ ብለን
ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን
አባባ አሉ ብለን

አበባ አየሽ ወይ ለምለም
አበባ አየሽ ወይ ለምለም
ባልንጀሮቼ ግቡ በተራ
እንጨት ሰብሬ ቤት እስክሰራ
እንኳን ቤትና የለኝም አጥር
እደጅ አድራለው ኮከብ ስቆጥር
ኮከብ ቆጥሬ ስገባ ቤቴ
ትቆጣኛለች የእንጀራ እናቴ
ለመስቀል ለታ ለደመራዉ
ንፍሮ ቀቅዬ ብላ ብለዉ
ጉልቻ አንስቶ ጎኔን አለዉ
ከጎኔም ጎኔን ኩላሊቴን
እማዬን ጥሯት መድሃኒቴን
እሷን ካጣችሁ መቀነቷን
አደይ የብር ሙዳይ ኮለል በይ
እቴ አበባሽ እቴ አበባዬ
አዬ እቴ አበባዬ
እቴ አበባሽ ስትለኝ ከርማ
አዬ እቴ አበባዬ
ጥላኝ ሄደች በሐምሌ ጨለማ
አዬ እቴ አበባዬ. . .




ምስል 4.16- በሴቶች የሚዘመር የአበባ የሽ ሆይ ምስል

## ምሳሌ 4.2

ከነሃሴ 13 እስከ መስቀል በዓል ድረስ በተለያዩ የሃገራችን ክፍሎች በወንዶች ልጆች የሚዘመር የቡሄ መዝሙር

ሆያ ሆዬ
ሆያ ሆዬ---ሆ
ሆያ ሆዬ---ሆ
እዚያ ማዶ---ሆ
ጭስ ይጨሳል---ሆ
አጋፋሪ---ሆ
ይደግሳል---ሆ
ያችን ድግስ---ሆ
ውጬ ውጬ---ሆ
ከድንክ አልጋ---ሆ
ተገልብጬ---ሆ
ያቺ ድንክ አልጋ---ሆ
አመለኛ---ሆ
ያለ አንድ ሰው---ሆ
አታስተኛ---ሆ
ሆያ ሆዬ ጉዴ ጨዋታ ነው ልማዴ (2 ጊዜ)
አውደ-ዓመት ዓመት ድገምና
ዓመት ድገምና
የእማምዬን ቤት ድገምና
ዓመት ድገምና
ወርቅ ይፍሰስበት ድገምና
ዓመት ድገምና
የአባብዬን ቤት ድገምና
ዓመት ድገምና
ወርቅ ይፍሰስበት ድገምና
ዓመት ድገምና. . .



ምስል 4.17 ሆያ ሆዬ የወንድ ልጆች ጨዋታ

## መልመጃ 4.9

- በአካባቢያችሁ በዘመን መለወጫ እና በበዓላት ወቅት የሚዘመሩ መዝሙሮችን በግልም ሆነ በቡድን በመሆን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ሃገረሰባዊ እውቀቶችን ያያሉ ያደንቃሉ። በተጨማሪም ተማሪዎች ስዕልን ፣ ሙዚቃን ፣ ትያትርን እና ስነ-ጽሁፍን ደጋግመው ሲለማመዱ የሚያገኙትን ጥቅም በስፋት ተመልክተናል። በዋናነት ተማሪዎች አንዳንድ ነገር በመለማመዳቸው የሚያገኙትን ጥቅም በዝርዝር ተወያይተናል። በመጨረሻም ተማሪዎች እምቅ ችሎታቸውን አውጥተው ለመጠቀም ብዙ ጊዜ መለማመድ ይገባቸዋል።

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የቤት አሰራር አይነቶችን ዘርዝሩ
2. በአካባቢያችሁ በበዓላት ወቅት የሚዘመሩ መዝሙሮችን ዘርዝሩ
3. በቤታችሁ የተለያዩ ፎቶዎችን በማንሳት ተለማመዱ
4. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን ዘርዝሩ
5. ትያትርን ወይም ድራማን ደጋግሞ መለማመድ የሚያስገኘውን ጥቅም ዘርዝሩ

# ምዕራፍ አምስት

# የትውን እና እይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማዛመድ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የእይታና የትውን ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለውን ዝምድና በስፋት እንመለከታለን፡፡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የእይታና የትውን ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ከፍተኛ ዝምድና አለው፡፡ የተለያዩ ዝርግ ቅርፆችን ከሂሳብ እና ማህበረሰባዊ ሳይንስ ጋር በማዛመድ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ ለማስቻል ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ የተለያዩ መዝሙሮችን አካባቢን ከማስዋብ እና ከማጽዳት ጋር በማያያዝ እንዲዘምሩ በማድረግ የተማሪዎችን አስተሳሰብ ሰፋ ለማድረግ ያግዛል፡፡

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ**

- የትውን እና እይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያዛምዳሉ
- የተፈጥሮ ቀለማትን በመመልከት መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን

ያዘጋጃሉ

- ዝርግ ቅርፆችን ከሂሳብ ትምህርት ጋር ያዛምዳሉ
- አካባቢን በማስዋብ እና በመንከባከብ ላይ መሰረት ያደረጉ ዝማሬዎችን ይዘምራሉ

## 5.1. የአይታና የትውን ጥበባት እርስ በርስ ያላቸው ዝምድና

### መግቢያ

በዚህ የትምህርት ክፍለጊዜ የእይታና የትውን ጥበባት ማለትም ሥዕል፣ ሙዚቃ ፣ ትያትር እንዲሁም ዳንስ ያላቸውን ዝምድና እንመለከታለን::

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች በሥዕል፣ በሙዚቃ፣ በትያትር እንዲሁም በዳንስ መካከል ያለውን ዝምድና ያጠናሉ

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች በሥዕል፣ በሙዚቃ፣ እንዲሁም በትያትር መካከል ያለውን ልዩነት ተናገሩ

### 5.1.1. ሥዕል ፤ሙዚቃ፤ እና ትያትር ያላቸው ዝምድና

በመሰረታዊነት ሥዕል ፤ሙዚቃ፤ ትያትር እንዲሁም ዳንስን ለመነጣጠል የሚከብዱ ብዙ ዝምድናዎች አላቸው:: ለምሳሌ የትያትር፣ የሙዚቃ እና የሥዕል መሰረትዊ አላባውያን ተቀራራቢ የሆነ የሃሳብ ግንኙነት አላቸው:: ለምሳሌ ቀለም፣ ውበት፣ ልዩነት ወዘተ የመሳሰሉ ነገሮች በትያትር፣ በሙዚቃ እና በሥዕል ውስጥ የምናገኛቸው መሰረታዊ ሃሳቦች ናቸው:: በዚህም መሰረት አብዛኞቹ የእይታና የትውን ጥበብ ሃሳቦች የሚወራረሱ ሆነው እናገኛቸዋለን::

አንድን የመድረክ ትያትር ብንመለከት ሥዕል ፣ ሙዚቃን እና ዳንስን በአንድላይ የያዘ ነው:: አንድ ትያትር ለተመልካች ከመቅረቡ በፊት የሚቀርብበት መድረክ በትክክል ከትያትሩ ጋር እንዲዛመድ ተደርጎ ዲዛይኑ ይሰራል:: ይህ የመድረክ ዲዛይን በአብዛኛው በሰዓሊ የሚሰራ ሲሆን በሥዕል፣ በቅርፃ-ቅርፅ፣ እንዲሁም

የተለያዩ አልባሳትን እና ቁሳቁሶችን ሰዓሊው በማዘጋጀት መድረኩ ለተመልካቾች ውብ እና ማራኪ ሆኖ እንዲታይ ያደርጋል:: በመቀጠል ሙዚቀኛው ደግሞ ከትያትሩ ጋር አብረው የሚሄዱ ሙዚቃዎችን በማዘጋጀት ትያትሩ በሚሰረበት ጊዜ ከመድረክ ጀርባ በመሆን ሙዚቃ መሳሪያዎችን ሊጫወት ይችላል ወይም በድምጽ ሊያዜም ይችላል:: በሶስተኛ ደረጅ በአንድ ትያትር ውስጥ ዳንስ ወይም ውዝዋዜ ይኖራል:: በዚህ ወቅት ትያትሩን የሚሰሩ ሰዎች ሊወዛወዙ ወይም ሊድንሱ ይችላሉ:: በአጠቃላይ በአንድ ትያትር ውስጥ የእይታ እና የትውን ጥበባት እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው የሚሄዱ የትምህርት አይነቶች እንደሆኑ ማሳየት እንችላለን::



ምስል 5.1- የትያትር መስሪያ መድረክ

## 5.2. የእይታና የትውን ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማገናኘት

### መግቢያ

በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች የተለያዩ ዝርግ ቅርፆችን እና ቅርፆችን ከሂሳብ እና ከሌሎች  የትምህርት አይነቶች ጋር በማዛመድ እንድንማር ለማድረግ ነው::

## ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

### ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኂላ

- ዝርግ ቅርፆች ከስዕል እና ከሂሳብ ትምህርት ጋር ያላቸውን ዝምድና ይረዳሉ
- ቅርፆች ሂሳብን ለመማር ያላቸውን ጠቀሜታ ይረዳሉ
- ዝርግ ቅርፆች ከማህበራዊ ሳይንስ ጋር ያላቸውን ዝምድና ያውቃሉ
- ለማህበራዊ ሳይንስ መማሪያ የሚያገለግሉ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን ያዘጋጃሉ
- የተውኔትን እና የማህበራዊ ሳይንስን ግንኙነት ያውቃሉ
- በአካባቢያቸው ያሉትን ነገሮች ወደ ተውኔት ይቀይራሉ
- የትውን ጥበባትን ከአካባቢ ሳይንስ ጋር ያዛምዳሉ
- ታሪካዊ ክንዋኔዎችን በተውኔት መልክ እንዲያሳዩ ያደርጋል
- ታሪካዊ አልባሳቶችን እንዲያዘጋጁ እና ታሪካቸውን እንዲያውቁ ያደርጋል

## የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት በሂሳብ መጽሃፍ ላይ ተስለው ያያችኋቸውን ዝርግ ቅርፆች ዘርዝሩ
- ተማሪዎች ካርታዎችን በየትኛው የትምህርት አይነት ላይ ተስለው እንደተመለከታችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ
- በአካባቢያችሁ አንድን ማህበረሰብ ለማበረታታት ወይም ለመቃወም የሚነገሩ እና ድራማ ሊሰራባቸው የሚችሉ ሃሳቦች ካሉ ለመምህራችሁ ተናገሩ


## 5.2.1. ዝርግ ቅርፆችን ፣ ቅርፆችን እና ቀለማትን ከሂሳብ ትምህርት ጋር ማዛመድ

ስለ ዝርግ ቅርፆች እና ቅርፆች ባህሪያት በምዕራፍ አንድ ላይ በስፋት ተመልክተናል:: በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በማዛመድ አንድነታቸውን በደንብ እንመለከታለን:: በሂሳብ ትምህርት ውስጥ

የሚገኘው ጂኦሜትሪ የሚያጠናው ስለዝርግ ቅርፅ እና ቅርፅ ሲሆን ስፋት ፣ ይዘት ፣ ዲያሜትር እንዲሁም ሬድየሱ ምን ያክል እንደሆነ በቁጥር ይገልጻል::

ስነ-ጥበብና ሂሳብ የቆየ ዝምድና አላቸው:: ከጥንታዊ የዋሻ ግድግዳ ላይ ስዕሎች ጀምሮ ጂኦሜትሪያዊ ዝርግ ቅርፆችን በተለያየ መንገድ ይጠቀማሉ:: በተጨማሪም ክፍልፋዮችን በስዕል ውስጥ ለማስቀመጥ እና ለማመጣጠን ሂሳባዊ ስሌቶችን ይጠቀማሉ:: ለዚህም ወርቃማ አወቃቀር (golden proportion) የምንለው በአንድ የመሳያ ወረቀት ወይም ግድግዳ ላይ እንዴት መቀመጥ አለበት የሚለውን የምናስቀምጥበት ቦታ ነው:: ጂኦሜትሪያዊ ቅርፆች ልክ እንደ ስዕል የሚጀምሩት ከነጥብ ወደ መስመር እንዲሁም ወደ ቅርጽ ያድጋል:: ጂኦሜትሪ ከስዕል በተጨማሪ ለኪነ-ህንፃ ትልቅ መነሻ ነው:: በአካባቢያችን አብዛኛዎቹ ህንፃዎች የተለያዩ ሰው ሰራሽ ቅርፆችን በመገጣጠም የሚሰሩ ናቸው::


ዝርግ ቅርፆች እና ቅርፆች በሂሳብ ክፍት እና ዝግ ተብለው ይጠራሉ:: በስዕል ዝርግ ቅርጽ የምንለው ሁል ጊዜ ዝግ ሲሆን (የአንድ መስመር ሁለት ጫፎች ሲገናኙ) ነው::



ምስል 5.2- ክፍት እና ዝግ ቅርጽ በሂሳብ


## ባር ግራፍ

ባር ግራፍ የተለያዩ አይነት መረጃዎችን ፣ መስመሮችን ፣ ቅርፆችን እና ነጥቦችን በመጠቀም ስዕላዊ በሆነ መንገድ ማሳየት ማለት ነው:: ባር ግራፍ በተለያዩ አመታት የተካሄዱ የከፍታ እና ዝቅታ መጠንን በእድሜ ደረጃዎች ፣ ያታ እና መጠን ለማነፃፀር ስዕላዊ በሆነ መንገድ የሚቀርብበት መንገድ ነው:: በዚህም መሰረት ተማሪዎች በሶስት የትምህርት አይነቶች ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ድረስ ያለውን መረጃ ለማነፃፀር በሚመች መልኩ የሲሊንደርን ቅርጽ በመጠቀም እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል::





ምስል 5.3 በዚህ ባርግራፍ ተማሪዎች ከ1-4ኛ ክፍል ያለውን የሂሳብ፣ የሳይንስ እና ስነ-ጥበብ ትምህርቶችን የውጤት ሁኔታ የሚያሳይ ነው

**በተጨማሪም ቅርፆችን በመጠቀም የተለያዩ ክፍልፋዮችን በፐርሰንት ለመግለፅ ያግዛል:: ከታች በቻርቱ ላይ የተመለከተው ከሰኞ-እሁድ በአንድ ሙዝየም ውስጥ ለመጎብኘት የመጡት ሰዎችን ብዛት በፐርሰንት ለማሳየት የተቀመጠ ሂሳባዊ ማሳያ ነው::**





ምስል 5.4- ዝርግ ቅርፆችን በመጠቀም የተለያዩ ክፍልፋዮችን ማሳየት

በጂኦሜትሪ ውስጥ ሁለት ዝርግ ቅርፆች ሲደራረቡ (የጋራ ጎን) ሲፈጥሩ የሚፈጠረውን ቅርጽ በመጠቀም የተለያዩ አይነት ዲዛይኖችን እንዴት መፍጠር እንደምንችል ማሳየት እንችላለን:: እነዚህንም ዲዛይኖች በልብስ ላይ ፤ በቤት ውስጥ ምንጣፎች ፤ እንዲሁም በበር እና መስኮት ላይ እናገኛቸዋለን::



ምስል 5.5- ክብ ቅርፆችን በመደጋገም የተለያዩ ዲዛይኖችን መስራት

ከላይ ያለውን ዲያግራም ተጠቅመን የአደይ አበባን ምስል ከታች እንደሚከተለው በትልቁ መስራት እንችላለን::



ምስል 5.6- ክብ ቅርፆችን በመጠቀም የተሰራ የአደይ አበባ ምስል

መልመጃ 5.1

◆ ተማሪዎች በሂሳብ ትምርት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቅርፃ ቅርፃችን በመጠቀም ዲዛይኖችን ስሩ

## 5.2.2.ስነ ጥበብ ከአካባቢ ሳይንስ ትምህርት እና ቀለማትጋር ያላቸው ዝምድና

ስነ-ጥበብ ከማህበረሰባዊ ትምህርቶች ጋር ሰፊ ዝምድና አለው። ማህበራዊ ሳይንስ የምንላቸው ታሪክን ፣ ተፈጥሯዊ ገፅታን እንዲሁም የሰዎችን ባህል እና የአኗኗር ሁኔታ ስዕላዊ በሆነ መንገድ ለማሳየት ይጠቅማል። የእይታ ጥበባት የተለያዩ ካርታዎችን ፣ በትንንሽ መጠን የተሰሩ ማሳያ ቅርጽ (ተምሳሌቶችን) እንዲሁም ቻርቶችን ለመስራት ይጠቅማል። ለምሳሌ የብዙ አፍሪካ ሃገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ የሃገራት ካርታዎች የተሸራረፉ የሚመስሉ (ተፈጥሮአዊ) ቅርፃች ናቸው። ስለዚህ ስለ ተፈጥሯዊ ቅርፃች ለመማር የተለያዩ ሃገራትን ቅርፅ ማየት በቂ ነው።



ምስል 5.7- የአፍሪካ ካርታ


ጠፍጣፋ ከሆነው የመሬት ካርታ በተጨማሪ የመሬትን እውነተኛ ቅርጽ በትንሹ ሰርቶ ለማሳየት ይጠቅማል፡፡ ስለዚህ የተለያዩ ነገሮችን ለማየት እንዲሁም ለማንቀሳቀስ በሚመች መልኩ በትንሹ ሰርቶ ማሳየት የተማሪዎችን ግንዛቤ ይጨምራል፡፡ የአክሱም ሃውልትን ከቦታው ድረስ ሄደን ማየት ባንችልም እንኳን በትምህርት ቤታችን ግቢ ውስጥ በትንሹ ሰርተን በማቆም ምን አይነት ገፅታ እንዳለው መመልከት እንችላለን ማለት ነው፡፡

የመሬትን ትክክለኛ ገፅታ (ልዑልን) ስንመለከት እያሽከረከርን በላዩ ላይ ባትሪ ወይም መብራት እያበራን ጨለማ እና ብርሃን እንዴት እንደሚፈጠር በደንብ ማየት እንችላለን፡፡




ምስል 5.8- ትክክለኛውን የመሬት ገፅታ የሚያሳይ ልዑል ቅርፅ ሲሆን ቀንና ማታ እንዴት እንደሚፈጠር የሚያሳይ ሞዴል

የተፈጥሮን ኡደት ለማሳየት የተለያዩ ቻርቶችን ሰርቶ ለማሳየት በጣም ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለምሳሌ ዝናብ እንዴት እንደሚፈጠር ለማሳየት መጀመሪያ የፀሀይ ሙቀት ከተለያዩ የውሃማ አካላት ላይ (ወንዝ ፣ ኩሬ ፣ ሃይቅ ፣ ውቅያኖስ) ሲያርፍ እና በትነት መልኩ እንዴት ወደ ደመና እንደሚቀየር እናሳያለን፡፡ ቀጥሎ በትነት መልክ የተሰበሰበው ደመና ቅዝቃዜን በመፍጠር ቀስ በቀስ ወደ ዝናብ ነጠብጣቦች ይቀየራል ማለት ነው፡፡ ይህንንም በስዕል መልክ እንደሚከተለው ልናሳይ እንችላለን ማለት ነው፡፡




ምስል 5.9- የዝናብ አፈጣጠር ኡደትን የሚያሳይ ምስል

በሌላ በኩል ስነ ጥበብ የድሮ አባቶቻችን የሰሩትን ታሪክ በስዕል መልክ ለአዲሱ ትውልድ ለማስተላለፍ ይጠቅማል። የአድዋ ጦርነትን ለዚህ ትውልድ ለማስተማር በስዕል ፣ በፎቶግራፍ ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል መልክ ልናቀርብ እንችላለን። ሆኖም ግን ለአዲሱ ትውልድ ተነሳሽነትን ለመፍጠር በተለያዩ ስዕሎች ማሳየት እንችላለን ማለት ነው። ለምሳሌ በሰዓሊ ተስፋየ ንጉሴ የተሳለው ቀጠሎ የተቀመጠው የአድዋ ጦርነትን የሚያሳየው ስዕል ሩቅ የሆነውን ዘመን በስዕል በቅርበት ጀግኖች አባቶቻችን እንዴት እንደተዋጉ እንድንመለከተው አግዞናል።



ምስል 5.10- የአድዋ ጦርነትን የሚያሳይ የቀለም ቅብ ስዕል

ስነ-ሰዕል የሰዎችን ዝግመተ-ለውጥ ሁኔታ ለማሳየት እንዲሁም የአስተሳሰብ ለውጦችን ለማሳየት ይጠቅማል:: ቀደምት የሰዎች የስልጣኔ ደረጃ ምን ይመስል እንደ ነበር እና አሁን ላይ ያለው ዘመናዊ ሰው ያለውን የሰውነት ቅርጽ ለመረዳትም ያግዛል::



ምስል 5.11- ጥንታዊ እና ዘመናዊ ሰዎች የነበራቸው የሰውነት አቋም


## መልመጃ 5.2

- ከላይ በምስሎች የተመለከትነውን መሰረት በማድረግ ሌሎች ለተፈጥሮ ሳይንስ መርጃ መሳሪያ ሊሆኑ የሚችሉ ስዕሎችን እና ዲያግራሞችን ስሩ

የተፈጥሮ ሳይንስ የምንላቸው የትምህርት አይነቶች ስለ ንጥረ ነገሮች ፣ ስለ ቁሳቁሶች ባህሪ እና የእንቅስቃሴ ሁኔታ ፣ እንዲሁም ስለ ከባቢ አየር ጸባይ ሁኔታዎች እና ባህሪያቸው የሚያጠና ነው:: ስለዚህ በዚህ ርዕስ ተፈጥሯዊ ነገሮች ከዕይታ ጥበብ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት እናጠናለን::

ጥበብ ሳይንስ ነው ወይም ሳይንስ ጥበብ ነው ስንል በመመራመር አዲስ ነገሮችን የምናገኝበት መንገድ ስለሆነ ነው:: ስለዚህ የሳይንስ እና የእይታ ጥበብን ነጣጥሎ ማየት የሚከብድ ነው:: አንድ የፈጠራ ስራ በተግባር ከመሰራቱ በፊት ስዕላዊ በሆነ መንገድ ይቀመጣል:: ለምሳሌ አውሮፕላን በተግባር ተሰርቶ ከመብረሩ በፊት አጠቃላይ ውጫዊ እና ውስጣዊ ገጽታው በስዕል ከተቀመጠ በኋላ ቀጣዩ የአውሮፕላን ክፍል መገጣጠም ይጀመራል ማለት ነው:: ለምሳሌ አውሮፕላን የመስራት ጽንሰ-ሃሳብ የተጀመረው ከአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን በፊት (ከዛሬ ስድስት መቶ አመታት በፊት) በጣልያናዊው ሰዓሊ ሊኦናርዶ ዳቬንቺ ሲሆን በተግባር የተሰራው ደግሞ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ (ከዛሬ

መቶ አስራ አምስት አመታት በፊት) በሁለት ወንድማማቾች ዊልቨር ራይት እና ኦሊቨር ራይት አማካኝነት ነው:: ከዚህ በመነሳት ስነ ጥበብ ከሳይንስ ጋር ከፍተኛ ግንኙነት እንዳለው መረዳት እንችላለን::



ምስል 5.12- የመጀመሪያው አውሮፕላን

መልመጃ 5.3

◆ ለተፈጥሮ ሳይንስ መማሪያ እና ማስተማሪያ የሚያገለግሉ የተለያዩ ስዕሎችን በመስራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ

## 5.2.3.የትወና ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለው ዝምድና

የትውን ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር የተዛመደ ነው:: የትወና ጥበብ ቋንቋን ፣ እንቅስቃሴን ፣ ሙዚቃን እና ውዝዋዜዎችን በአንድ ላይ ያያዘ ነው:: በአንድ ተውኔት ውስጥ የሚገኙ ገፀ-ባህሪያት የሚመረጡት ከተለያየ የሙያ መስክ ስለሆነ የማህበረሰቡን የእለት ከእለት ክንዋኔዎች ለታዳሚዎች በሚመጥን መልኩ በማቅረብ ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ:: ስለዚህ በአንድ ተውኔት ውስጥ ዶክተር ፣ ኢንጅነር ፣ መምህር ... ወዘተ የሙያ አይነቶች በማካተት ብዙ አይነት ሙያዎችን ልናሳይ እንችላለን ማለት ነው:: አንድ ተዋናይ የታሪክ መምህርን ገጸ-ባህሪ ወክሎ ለመጫወት ቢፈልግ ታሪክን በሚገባ ማወቅ ይጠበቅበታል:: የሚሰራው ገፀ-ባህሪ የነበረበትን ዘመን ፣ የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም ቦታውን በትክክል በመጥቀስ ልናሳይ እንችላለን ማለት ነው:: የትወና ጥበብን ከማህበራዊ ሳይንስ ጋር በማገናኘት ድራማዎችን ፣

ቲያትሮችን መነባብቦችን ፣ ቀረርቶ እና ሽለላዎችን እንዲሁም ውዝዋዜዎችን ማሳየት እንችላለን፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርቶችን ለማስተማር ተውኔት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ተማሪዎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች የሚመለከቷቸውን የሰዎች እንቅስቃሴዎችን በግለ-ተውኔት ፣ በፓንቶ ማይም ወይም በትያትር መልክ ማሳየት ይቻላል ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ የበዓል አከባበሮችን እንዲሁም በጋራ የተለያዩ ተውኔቶችን ማሳየት ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ የዳውሮን የዘመን መለወጫ ቶኪቢአ ፣ የጋሞን ዮ-ማስቃላ ፣ የወላይታን ጊፋታ ፣ የአሪን ዲሽታ ጊና … ወዘተ የሚደረጉ የበዓል አከባበር ስርዓቶችን ድራማዊ በሆነ መንገድ መግለጽ እንችላለን፡፡ ስለዚህ በአካባቢያችን የሚገኙ አበይት የበዓል አከባበሮችን መነሻ በማድረግ የሰዎችን እንቅስቃሴ ፣ የሚጠቀሙባቸውን ቁሳቁሶች በመጠቀም በግለ ተውኔት ወይም በድራም መልክ መግለጽ እንችላለን፡፡

ተውኔቶች የራስችንን እምቅ ችሎታ ከማሳደግ በተጨማሪ ማህበራዊ መስተጋብርንም ያሳድጋል፡፡ በአንድ ድራማ ሁለት እና ከዚያ በላይ ሰዎች ሊሳተፉበት ይችላሉ፡፡ ከብዙ ሰዎች ጋር አብረን በሰራን ቁጥር ከሰዎች ጋር መግባባትን ፣ አብሮ መስራትንና ተሳትፎን ይጨምራል፡፡ ስለዚህ ከተለያዩ ሰዎች ወይም ተማሪዎች ጋር ድራማም ሆነ ትያትር ስንሰራ አዳዲስ እውቀትን እና ልምድን እንቀስማለን፡፡

የተፈጥሮ ሳይንስ ከተፈጥሮ ሳይንስ ጋር ያለውን ዝምድና ስንመለከት ከህክምና ፣ ከኢንጅነሪንግ እንዲሁም ፊዚክስ ትምህርቶች ዳር በማገናኘት መስራት እንችላለን፡፡ ትያትር የገሃዱ አለም ነጸብራቅ መበሆኑ ለተመልካች በሚመጥን መልኩ ከሽኖ ማቅረብ ነው፡፡ አንድ ድራማ ውስጥ የሂሳብ መምህር ገጸ-ባህሪ ቢኖር እርሱ የሚያከናውናቸውን ተግባራት በማጥናት ተውኔቱ ይሰራል ማለት ነው፡፡ የቃላት አጠቃቀም ፣ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን ፣ የእጅ ጹሑፍን እንዲሁም ሌሎች ባህሪያትን በትክክል ለተመልካች ለማሳየት ይጠቅማል፡፡

ታሪካዊ ክንውኖችን ለተመልካቾች በሚመች መልኩ የተለያዩ አልባሳቶችን በመጠቀም ማሳየት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ የነገስታቶችን ታሪክ ማለትም የወላይታን ንጉስ ካዎ ጦናን ፣ የሲዳማን ንግስት ፋራን ፣ የኮንሶን ጎሳ መሪ ቦቆላን ፣ የዳውሮን ንጉስ ካኦ ሃላላን … ወዘተ ታሪክ በመውሰድ በትያትር

እና በድራማ መልኩ ብናቀርብ ተመልካቾች ከመዝናናት በተጨማሪ ታሪክም ያውቃሉ:: ስለ ነገስታት ድራማ ስንሰራ ትክክለኛው አልባሳት ምን ይመስል እንደነበርና ምን አይነት እንቅስቃሴዎችን ያሳዩ እንደነበር ለማስረዳት ያግዛል:: ለምሳሌ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ፓንቶ ማይምን በመጠቀም ያለ ንግግር የነገስታቶችን የሰውነት እንቅስቃሴ እና የአለባበስ ሁኔታ ማሳየት ይቻላል:: ቀደምት አባት አርበኞቻችንን እንቅስቃሴ እና አልባሳቶችን በመልበስ መከወን አንዱ መንገድ ነው::



ምስል 5.13- የከፋው ንጉስ ጋኪ ሻሪቾ አለባባስ

መልመጃ 5.4

- ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የምታውቁትን ታሪካዊ እና ባህላዊ ክንዋኔ በመውሰድ በቡድን በቡድን በመሆን ተውኔት/ድራማ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ

## 5.2.4. ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች ሙዚቃን ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር እንደሚገናኝ

በሚገባ ይረዳሉ

- ሙዚቃን ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማዛመድ ዜማዎችን እና ውዝዋዜዎችን ያከናውናሉ
- ቃላትን ማስታወስ የማይችሉ ተማሪዎች ታዋቂ የዘፈን ግጥሞችን በማጥናት የማስታወስ ክህሎታቸውን ያሳድጋሉ::

## የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት በነበሩ የሙዚቃ ትምህርቶቻችሁ ላይ ስለ ተለያዩ የትምህርት አይነቶች የዘመራችኋቸውን መዝሙሮች በማስታወስ በዜማም ሆነ በግጥም ለመምህራችሁ ተናገሩ

በዚህ ርዕስ ተማሪዎች ሙዚቃ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለውን ዝምድና ትማራላችሁ:: ስለዚህ ሙዚቃ ከሂሳብ፣ ከተፈጥሮ ሳይንስ እንዲሁም ከህብረተሰብ ሳይንስ ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድና ከዜማ እና ከውዝዋዜ ጋር በማዋሃድ ትከውናላችሁ::

ሙዚቃ የአለም ቋንቋ ነው ስንል ያለ ምክንያት አይደለም:: ሙዚቃ አብዛኛውን የአለማችንን ክፍል ያግባባል ያስደስታል እንዲሁም ስሜት ለመግለጽ ያግዛል:: በተመሳሳይ የሙዚቃ ትምህርትን ከሁሉም የትምህርት አይነቶች ጋር በማገናኘት ለህፃናት ማስተማሪያ አይነተኛ መንገድ ነው:: ሙዚቃን እንደ ማህደረ ትውስታ መጠቀም ጠቃሚ የማስተማሪያ መንገድ ሊሆን ይችላል ለምሳሌ ስለ ሂሳብ ፣ ስነ ህይወት ፣ ስነ-ምግባር ፣ ስፖርት ፣ አከባቢ ሳይንስ ወዘተ ያካትታል::

### ሀ. ሙዚቃ ከሂሳብ ትምህርት ጋር ያለው ዝምድና

ሙዚቃን ከሂሳብ ትምህርት ጋር በማገናኘት ስለ ቁጥሮች እና መሰረታዊ የሂሳብ ስሌቶችን ማስተማር እንችላለን:: ለምሳሌ ሙዚቃ ከሂሳብ ትምህርት ጋር ስናገናኘው ስለመደመር ፣ መቀነስ ፣ ማባዛት ወይም ማካፈል ሙዚቃን ልንጠቀመው እንችላለን::

ምሳሌ፡-

**አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች**

አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ

ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ዘጠኝ ይቀራል
ዘጠኝ አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበርነ ስምንት ይቀራል
ስምንት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሰባት ይቀራል
ሰባት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ስድስት ይቀራል
ስድስት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር አምስት ይቀራል
አምስት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር አራት ይቀራል
አራት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሦስት ይቀራል
ሦስት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሁለት ይቀራል
ሁለት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር አንድ ይቀራል
አንድ አረንጓዴ ጠርሙስ በግድግዳ ላይ
ድንገት እሱ ወድቆ ቢሰበር ዜሮ ይቀራል

### መልመጃ 5.5

- ተማሪዎች በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች የሚዘመሩ መዝሙሮችን በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡላቸው

## ለ. ሙዚቃን ከሳይንስ ትምህርት ጋር በማገናኘት መዘመር

ሙዚቃን ከግልና ከአካባቢ ንፅህና ጋር በማዛመድ የግልና የአካባቢያችንን ንፅህና እንዴትና በምን ሁኔታ መጠበቅ እንዳለብን ፣ ስለ እርሻ በሙዚቃ እንዴት ማወቅ እንዳለብን ፣ ሙዚቃን ከተፈጥሮ ጋር በማዛመድ ስለ ተፈጥሮ በመዘመር በሚገባ ልንረዳው እንችላለን። ሙዚቃን ከተለያዩ እንስሳት እና

አዕዋፋት ጋር በማዛመድ ስለ ሀገር ፍቅር ፣ ስለቤተሰብ ፍቅር ልንማር እንችላለን። በአጠቃላይ በሙዚቃ ስለ ተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች እንማራለን።

**ምሳሌ**

ተማሪዎች ስለ ንጽህና በሳይንስ ትምህርት ውስጥ ሊዘምሩ ይችላሉ

**ሳይንስ ሳይንስ**

ሳይንስ ሳይንስ መድሀኒቴ
ያስተማረኝ ጤንነቴን
ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን ስበላ
ለትምህርት ስሄድ ሳይንስ ላጠና
እጄን ታጥቤ ምሳ ስበላ
ደግሞ ይታየኛል የሳይንስ መላ
እግሬን ታጥቤ ማታ ስተኛ
በህልሜ ታየኝ ሳይንስ ሳጠና

**መልመጃ 5.6**

◆ ተማሪዎች በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች የሚዘመሩ መዝሙሮችን በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡላቸው

## ሐ. ተማሪዎች በየቀኑ የሚያደጓቸውን ድርጊቶች በመዝሙር መግለጽ

### መግቢያ

የሰው ልጆች በተለምዶ ማንኛውንም ስራ በሚሰሩበት ወቅት እንቅስቃሴ በማድረግ እና መዝሙሮችን በመዘመር (ሙዚቃ በማዳመጥ) የትኛውንም ዓይነት ስራን ሊከውኑ ይችላሉ። ከእነዚህም ስራዎች መሃል ለአብነት ያህል ፊታቸውን ሲታጠቡ መዝሙሮችን ይዘምራሉ የቤታቸውን ፣ የአካባቢያቸውን ፣ የመስሪያ ቤታቸውን ቁሳቁሶች ሲያፀዷቸው መዝሙሮችን በመዘመር ይከውኑታል በተጨማሪም አካባቢያቸውን ሲያፀዱም መዝሙሮችን እየዘመሩ ያፀዱታል ይህንንም የሚያደርጉት የሚሰሩትን ስራ ስለሚያፈጥንላቸው ወይም አእምሯቸውን ነፃ አድርገው ስራቸውን ለመከወን ሲፈልጉ ነው።

## ማነቃቂያ

♣ በቤታችሁ ስራን በምትሰሩበት ወቅት ምን በማድረግ ስትሰሩ ያስደስታችኋል?

## ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች በቤታቸውና በአካባቢያቸው ስራን በሚሰሩበት ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይረዳሉ

### ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት

ፊታችን እንታጠብ እንታጠብ እንታጠብ
ፊታችን እንታጠብ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት
ጥርሳችንን እንቦርሽ እንቦርሽ እንቦርሽ
ጥርሳችን እንቦርሽ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት
ፀጉራችንን እናበጥር እናበጥር እናበጥር
ፀጉራችንን እናበጥር ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት
ልብሳችንንም እንልበስ እንልበስ እንልበስ
ልብሳችንንም እንልበስ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት
ቁርሳችንንም እንብላ እንብላ እንብላ
ቁርሳችንንም እንብላ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት
ትምህርት ቤትም እንሂድ እንሂድ እንሂድ
ትምህርት ቤትም እንሂድ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት

## መልመጃ 5.7

◆ ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የሚታወቁ ተጨማሪ ስለ ጽዳት የተዘመሩ መዝሙሮች ካሉ በክፍል ውስጥ ዘምሩ

## መ. ስለ አካባቢያዊ ቀለማት፣ ዕጽዋትና እንስሳት መዘመር

## መግቢያ

ከዕፅዋትና እንስሳት እንቅስቃሴ የተለያየ አይነት ውዝዋዜዎችን ማስመሰል

እንችላለን። እፅዋቶች ንፋስ ሲነፍስ ወደተለያየ አቅጣጫ ከፍና ዝቅ እንዲሁም ወደ ጎን ይወዛወዛሉ። የተለያዩ አይነት እንስሳቶችም በሚራመዱበት ጊዜ እና በሚሮጡበት ጊዜ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያሳዩናል። የሰው ልጆችም የዕፅዋቶችን እና እንስሳቶች እንቅስቃሴን በመከወን የተለያዩ ውዝዋዜዎችን መወዛወዝ ይችላሉ።

## ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች ከተለያዩ ዕፅዋትና እንስሳት እንቅስቃሴ ውዝዋዜን ይማራሉ

## ማነቃቂያ

- የተለያዩ መዝሙሮችን እየዘመራችሁ የዕፅዋትን እና የእንስሳትን እንቅስቃሴ በማስመሰል ውዝዋዜዎችን ስሩ

ከዕፅዋትና እንስሳት እንቅስቃሴ የተለያዩ አይነት ውዝዋዜዎችን ማስመሰል እንችላለን። እፅዋዕቶች ንፋስ ሲነፍስ ወደ ተለያየ አቅጣጫ ከፍና ዝቅ እንዲሁም ወደ ጎን ይወዛወዛሉ። የተለያዩ አይነት እንስሳቶችም በሚራመዱበት ጊዜ ፣ በሚሮጡበት ጊዜ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያሳዩናል። የሰው ልጆችም የዕፅዋቶችን እና የእንስሳቶችን እንቅስቃሴ በመከወን የተለያዩ ውዝዋዜዎችን ማስመሰል ይችላሉ።

### መልመጃ 5.8

- ተማሪዎች ስለ ዛፎች ፣ ስለ አበቦች እና ወንዞች በባህላችሁ የሚታወቁ መዝሙሮችን ከምትዘምሩለት ነገር እንቅስቃሴ ጋር በማዛመድ አሳዩ

## 5.2.5.ገጸ-ባህሪያትን መጫወት

ገጸ-ባህሪ በአንድ ተውኔት ወይም ድርሰት ውስጥ የሚገኝ የተውኔት ክፍል ነው። ገጸ-ባህሪ በአንድ ተውኔት ወይም ድራማ ውስጥ ያሉ የሰዎችን ባህሪ የሚያሳዩ ክንዋኔዎች ናቸው። በአንድ ተውኔት ውስጥ የተለያዩ አይነት ገጸባህሪያት ቢኖሩም በዋናነት ግን ወጥ እና አስተኔ ገጸ-ባህሪያት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ተውኔት በመድረክ ላይ ተመልካቾችን በቀጥታ በማግኘት የሚከውን ጥበብ ነው። ተውኔት ፣ ፅሁፈ ተውኔት ወይም ድርሰት የተፃፈውን የምናብ ድርሰት ታሪክ ገፀ-ባህሪ እና ድርጊቶችን ጨምሮ ህይወት የምንዘራበት

ሂደት ነው፡፡ ተውኔት በመድረክ ላይ ወደ አፈፃፀም የሚቀየር የስድ ወይም የግጥም ጥንቅር ነው፡፡ ታሪኩ በባህሪያቱ መካከል ባለው መስተጋብር የሚገፋ እና ለተመልካች በመልእክት በትግበራ የሚበቃ ነዉ፡፡ ተውኔት በንግግር ውይይት ላይ በእጅጉ የተመረኮዘ ነው፡፡

## ሀ. አስተኔ ገጸ-ባህሪ

አስተኔያዊ ገጸ-ባህሪያት የሚባሉት በአንድ ተውኔት ለተመልካች ይፋ የሚሆኑ የመጀመሪያ ገጸ-ባህሪያት ሆነው አጭር ቆይታ ብቻ የሚኖራቸው ናቸው፡፡ ለዚህም ከመድረክ ጀርባ የሚሰሙ ድምፆች ፣ ከተዋናዩ በስተጀርባ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ የሚያሳዩ እንዲሁም በአጃቢነት የሚታዩ ሰዎች ናቸው፡፡

## ለ. ወጥ ገጸ-ባህሪ

ወጥ ገጸ-ባህሪ ማለት በአንድ ተውኔት ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ባለው የታሪኩ ክፍል ውስጥ የሚቀጥል የገጸ ባህሪ አይነት ነው፡፡ ስለዚህ ወጥ ገጸ-ባህሪ በአንድ ተውኔት ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ ተደጋግሞ በመምጣጥ የተውኔቱን ብዙ ክፍል የሚሸፍን ነው፡፡ ወጥ ገጸ-ባህሪያት በሁለት መልኩ ሊተወኑ ይችላሉ፡፡

## አቀንቃኝ ወጥ ገጸ-ባህሪያት

አቀንቃኝ ገጸ-ባህሪያት የምንላቸው የታሪኩ መሪ ተዋንያኖች ሲሆኑ በታሪኩ ውስጥ የያዙትን ዓላማ ለማሳካት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በአንድ ድራማ ውስጥ የፖሊስን ገጸ-ባህሪ ይዞ የሚጫወት ሰው አንድን ሌባ ለመያዝ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እስከ ድራማው መጨረሻ ድረስ በታሪክ ውስጥ ይዞ ይቀጥላል፡፡

## ጸረ-አቀንቃኝ ወጥ ገጸ-ባህሪያት

ጸረ-አቀንቃኝ ገጸ-ባህሪያት የአቀንቃኝ ገጸ-ባህሪያት ተቃራኒ ሲሆን የሌሎችን ዓላማ እንዳይሳካ ለማድረግ የሚጫወቱት ተውኔት ነው፡፡ ለምሳሌ ፖሊሱ ሌባውን ለመያዝ ጥረት ሲያደርግ ሌባው ደግሞ ከፖሊሱ ለማምለጥ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ የሚያሳይ ነው፡፡

## መልመጃ 5.9

◆ ተማሪዎች የተለያዩ ወጥ-ገጸባህሪያትን እና አስተኔያዊ ገጸ-ባህሪያትን በመላበስ ተጫወቱ

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የትውን እና እይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለውን ዝምድና በሰፊው ተመልክተናል:: ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ተውኔት ከትምህርቱ በተጨማሪ ሌሎች የትምህርት አይነቶችን በማያያዝ የፈጠራ እና የማመዛዘን ችሎታን ለመጨማር ያግዛል:: ለምሳሌ ስዕል የተለያዩ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ለመስራት ፣ ካርታዎችን ለማዘጋጀት እንዲሁም ታሪካዊ ክንዋኔዎችን በፎቶ እንዲሁም በተንቀሳቃሽ ምስል መልክ ለማሳየት ያግዛል:: መዝሙሮችን በመጠቀም ሂሳብን ፣ ሳይንስን እና አካባቢን ለመጠበቅ የሚያግዙ እንቅስቃሴዎችን ማስተለለፍ እንችላለን ማለት ነው:: በአጠቃላይ የትውን እና የእይታ ጥበባት በማህበረሰቡ ወስጥ ያሉ ልዩ ልዩ ክንዋኔዎችን አጭር እና ግልጽ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ያግዛሉ:: የትውን ጥበባትን ከማህበራዊ እንዲሁም ከተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርቶች ጋር በማዛመድ ተውኔቶችን በማዘጋጀት ለተመልካች በማቅረብ የምንፈልገውን ሃሳብ ማስተላለፍ እንችላለን::

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. የእይታ ጥበብ ከሂሳብ ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድና በስዕል ግለጹ
2. የእይታ ጥበብን በመጠቀም በማህበራዊ ሳይንስ ጉዳይ ላይ ምን አይነት ስዕሎችን ልንሰራ እንችላለን?
3. የ4ኛ ክፍል የሙዚቃ እና የሂሳብ ትምህርት ያላቸውን ዝምድና ግለጽ
4. ትያትር ልንሰራባቸው የምንችላቸው ታሪካዊ ክስተቶች ምን ምን ናቸው?

# ዋቢ መጽሀፍት

## የታተመ


1. Mihiretu wassie (2010 E.C). Drawing, Arba Minch College of Teachers' Education, student module አርባ ምንጭ
2. Fikadu Dejene (2011). Painting, Arba Minch College of Teachers' Education, student module አርባ ምንጭ


## መጽሀፍ


1. ሁሴን ጀማል (2001 ዓ.ም). ፕሮፌሽናል የካሜራ ጥበብ ፤ ነቢያት መጽሀፍት መደብር ፤ አዲስ አበባ
2. ጳውሎስ ኞኞ (1984). አጼ ምኒልክ ፤ አዲስ አበባ
3. 3D total publishing (2013). Art Fundamentals,
4. Beverly Johnson (2019). Drawing characters, Impact books